# ፫

## በማስተዋል ማንበብ (2)

### በቃላት የተወከሉ ሐሳቦች

ምንም እንኳ መጽሐፍ ቅዱስን በምናነብበት ጊዜ ታሪክ፥ መልክዐ ምድር፥ ባህል፥ ጸሐፊው፥ አወቃቀርና የሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽ የመሳሰሉት ነገሮች ባለማቋረጥ በአዕምሯችን ውስጥ ቢኖሩም፥ በመጨረሻ ትልቁን ትኩረት የምንሰጠው ለቃላት ነው። የፈለግነውን ዐይነት ቋንቋ ብንናገርም፥ ሐሳባችንን የምንገልጸው በቃላት አማካይነት ነው። እነዚህን ሐሳቦች በትክክል መግለጽ ከፈለግን ትክክኛ በሆኑ ቃላት መጠቀም አለብን።

ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ በጊዜው የተገለገለባቸው ቃላት እግዚአብሔር ለመናገር የፈለገውን ስለሚናገሩ ጠቃሚዎች ናቸው። የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ይህን አካሄድ ያስተውላሉ፤ ስለዚህም የሚያቀርቡትን ትምህርትም ሆነ ክርክር የሚመሠርቱት በተመረጡ ቃላት ላይ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን መንገድ በዘፍጥረት 12፥7 ላይ፥ እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለዘሩ ስለ ሰጠው ተስፋ የሚናገረውን በገላትያ 3፥16 ላይ በመጥቀስ ተጠቅሞበታል። በዘፍጥረት ውስጥ፥ በዕብራይስጡ «ትውልድ» የሚለው ቃል «ልጆች፥ ዘር» ተብሎ ተተርጕሟል። ቃሉ ነጠላ እንጂ ድርብ፥ አንድ እንጂ ብዙ አይደለም። ሐዋርያው ጳውሎስም ይህንኑ አጠናክሮ ሲያስረዳ ተስፋው ፍጻሜ የሚያገኘው በመላው ሕዝብ ሳይሆን በአንድ በተለየ ሰው፥ ይህም ሰው ኢየሱስ እንደ ሆነ ያረጋግጣል።

እንዲህ ሲባል ግን የመጽሐፍ ቅዱስ ንባባችን ቃል በቃል መሆን አለበት ማለት አይደለም። ቃላት የሚያገለግሉት ዐረፍተ ነገሮችን ለመመሥረት ሲሆን ጥቅማቸውም የሚታወቀው በሚገልጹት ሐሳብ ነው። ስለዚህ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን የቃል በቃል ትክክለኛ መንገዱን ሳይከተሉ ሊጠቅሱ ይችላሉ። ለቃሉ እምብዛም ትኩረት ሳይሰጡ ትርጕሙን ይጽፋሉ። ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 11፥8 ላይ፥ ኢሳይያስ 29፥10ንና ዘዳግም 29፥4 አጣቅሶ በራሱ ነጻ አስተሳሰብ በጻፈ ጊዜ ያደረገው ይህንኑ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስን በራሳችን ቋንቋም ሆነ ከጥንቱ ቋንቋዎች በአንዱ፥ ማለትም ብሉይ ኪዳንን በዕብራይስጥ፥ አዲስ ኪዳንን በግሪክ ብናነብ፥ እንደ ጽሑፉ ዐይነትና ስልት እንዲሁም፥ እንደ ጸሐፊው ዓላማ የትርጕሙ መጠን በርዝማኔው የተለያየ እንደሚሆን ማወቅ አለብን፤ ይህም በአንድ ወይም በሁለት ቃላት ምክንያት ሊሆን ይችላል። በሌሎች አካሄዶች ደግሞ የትርጕሙ መጠን ወይም ስፋት ብዙ ዐረፍተ ነገሮችን ሊይዝ ስለሚችል ነው። በማንኛውም ጊዜ ግን ሁለት

ነገሮችን በአዕምሯችን ውስጥ መያዝ አለብን፥ እነርሱም እንደኛው የቃላቱ ትርጉም የሚፈስሰው በዐረፍተ ነገሩ ውስጥ በሚገኘው ምንባብ ሲሆን የዐረፍተ ነገሩ ትርጉም የሚወሰነው ደግሞ በዚያ ውስጥ በሚገኙ ቃላት ነው።

## ስድ ንባብና ግጥም

አንድ ማእከላዊ ሐሳብ ረዘም ባለ ቅርጽ እንዴት ሊገለጽ እንደሚችል የዕብራይስጡ ሥነ ግጥም ማለፊያ ምሳሌ ነው። የግጥሙ ትርጉም የሚገኘው በእያንዳንዱ ቃል ውስጥ ሳይሆን፥ የጸሐፊውን ሐሳብ የሚገልጹትን የተወሰኑ መሥመሮችን (ስንኞችን) ወይም ዐረፍተ ነገሮችን በመመልከት ነው። የግጥሙን ሐሳብና ውጤት ለመግለጽ ሲባል ቃላቱና ሐረጉቹ በጥንቃቄ የተዋቀሩ ናቸው።

ለምሳሌ አንዱ ስንኝ ዋናውን ሐሳብ ሲገልጸው ሁለተኛው ስንኝ ደግሞ በጥቂት ልዩነት ያንኑ ሐሳብ ይደግመዋል። ወይንም በተጓዳኝ «ጥበብን ማግኘት ምንኛ ከወርቅ ይሻላል! ማስተዋልንም ማግኘት ከብር ይልቅ የሚመረጥ ነው»፤ (ምሳሌ 16፥16) እያለ ይጽፋል። በሌላ ሁኔታ ደግሞ እኛ መዝሙር በምንዘምርበት ጊዜ አዝማቹን እንደምንደጋግመው ዐይነት፥ አንድ ጥቅስ እንደ አዝማች ሆኖ ይደጋገማል፤ (ለምሳሌ መዝ 42፥5 እና 11)። ከዕብራይስጡ ግጥም ብዙ ልዩ ባሕርያት መካከል ሁለቱ ድግግሞሽና ተመሳሳይ ናቸው፤ ትርጉማቸውን መገንዘብ ከፈለግን ግን የቃላቱን አወቃቀር ማወቅ አለብን። ስለዚህ የምናነበውን የጽሑፍ ዐይነት ማወቅ ያስፈልገናል።

አብዛኛው ብሉይ ኪዳን (በተለይም የመዝሙር መጽሐፍ፥ አብዛኛው የነቢያትና የጥበብ ሥነ ጽሑፍ) የተጻፈው በግጥም አጻጻፍ በመሆኑ ለመረዳት ከፈለግን እንደ ግጥም አድርገን ልንገነዘበው ይገባል። ለምሳሌ እኔ ገጣሚ ነኝ ልበል፥ ስለዚህ ውስጣዊውን ስሜቴንና የጠለቀ ሐሳቤን ለመግለጽ ግጥም ጻፍሁ፤ የስድ ውጤት እንዲያመጣ አስቤ ቃላትን በጥንቃቄ በመምረጥ ግጥሜን አዘጋጀሁ፤ የስድ ንባብን የአጻጻፍ ዘይቤ፥ መመሪያ አልተከተልሁም፤ ለስድ ንባብ የአጻጻፍ ዘይቤ በማይስማሙ፥ በተለያዩ ሥዕላዊ ቃላት፥ ምልክቶች የሐሳብ መግለጫዎችና ዘይቤዎች ተጠቀምሁ።

ነገር ግን አንድ ሰው፥ አንድ ቀን ይህን ግጥም አንሥቶ ግጥሙን እንደ ግጥምነቱ ሳይሆን፥ ልክ ከአንድ ጋዜጣ ከመጀመሪያው ገጽ ላይ እንዳገኘው ዜና ቢያነበው፥ የጽሑፉን ሐሳብ አይገነዘበውም፤ እኔንም ቅር ያሰኘኛል። እኔ ግጥም ብጽፍ አንባቢው ግጥሜን እንደ ግጥም እንዲያነብልኝ እፈልጋለሁ። በተመሳሳይ ሁኔታ የመጽሐፍ ቅዱስ ገጣሚም ግጥሙን እንደ ግጥም እንድናነብለት ይፈልጋል። ይሁን እንጂ ክርስቲያኖች አብዛኛውን ጊዜም ግጥሙን እንደ ስድ ንባብ ያነቡታል። ይህን በሚያደርጉበት ጊዜ ደራሲው ሊል የፈለገውን ሐሳብ

በራሳቸው ዘይቤ ይተረጉሙታል፤ ከሁሉም የባሰውና አስከፊው ነገር የጸሐፊውን ስሜትና ዓላማ ጨርሰው ይስቱታል።

## የቃላት አገባብ

ስለ ቃላት ምንነት ለማወቅና አገባባቸውንም ተረድቶ ለመጠቀም የሚያግዘን የቃላት ዝርዝር መጸሐፍ (ኮንኮርዳንስ) ነው። የተሟላ መዝገበ ቃላት እያንዳንዱን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በፊደል ተራ ቅደም ተከተል የያዘ ነው። ተጨማሪ የቃላት ዝርዝር ማብራሪያ ያለው መዝገበ ቃላት የዕብራይስጡንም ሆነ የግሪኩን ቃል አተረጓጐም ያሳያል። እነዚህ የቃላት ዝርዝር መጻሕፍት ምናልባትም የዕብራይስጡንም ሆነ የግሪኩን ቃላት በፊደል ቅደም ተከተል ያካተቱ ሊሆኑ ይችላሉ። መግለጫዎቹ አንባቢው ወይም አጥኚው ሰው በማጣቀሻውና በመዝገበ ቃላቱ እንዴት አድርጎ መጠቀም እንዳለበት ይናገራሉ።

ምንም እንኳን የቃላትን ዝርዝር የያዘ መጽሐፍ ጠቃሚነቱ ባይካድም፥ ቃላቱ በየት ስፍራ በጥቅም ላይ እንደሚውሉ ከማመልከት ወዲያ የሚያደርገው ነገር የለም። ቃላት እንዴት ተደርገው በተግባር ላይ እንደሚውሉ አያስረዳንም። አንድ ቃል በየት ስፍራ ሊጠቅም እንደሚችል ለመወሰን ስለ እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ግንዛቤ ሊኖረን ይገባል፤ ያለዚያ ስሕተት ላይ እንወድቃለን። ቃል በአንድ ስፍራ የሚቆም ወይም በዘፈቀደ በጥቅም ላይ የሚውል ነገር አይደለም። የተወሰነ ዋጋ ወይም ውክልና እንዳለውና ከዚያ በላይ እንደማይሄድ እንደ ቊጥርም አይደለም፤ የቃል ትርጒም ይለዋወጣል፤ አገባቡም እንዲሁ የሚለዋወጥ ሆኖ እናገኘዋለን።

## የተለያዩ ፍችዎች

ቃል ወይም ሐረግ በተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ የተለያዩ ፍችዎች ቢኖሩት ልንደነቅ አይገባንም፤ ይህ የቋንቋ ባሕርይ አንዱ ክፍል ነው። ምንጊዜም የቃልን ወይም የሐረግን ትርጒም መወሰን የሚቻለው ጸሐፊው በተጠቀመበት ሁኔታ መሆን እንዳለበት ማስተዋል ይገባናል። ቃላት የዐረፍተ ነገር ክፍሎች ናቸው፤ ዐረፍተ ነገር ደግሞ የአንቀጽ ክፍል፥ አንቀጽም የመጽሐፍ ክፍል ነው። እነዚህ ሁሉ ቃላቱ የሚገኙበትን ዐውድ ይመሠርታሉ። የዚህን ዐውድ ወይም ጭብጥ ካላወቅን ትርጒሙን ለመገንዘብ አስቸጋሪ ይሆንብናል።

ለምሳሌ:- «ወደ ግራ ፈቀቅ አለ» ቢል ይህ ቀጥተኛ ዐረፍተ ነገር ነው፤ ነገር ግን ከአንድ በላይ ትርጒም ሊኖረው ይችላል። ስለዚህ ትርጒሙ አንድ ሰው በአጠገቡ እንዲያልፍ ወደ ጐን ፈቀቅ አለ ያሰኛል፤ ወይም በፖለቲካ አስተሳሰቡ ላይ ለውጥ አደረገ ማለትም ይሆናል። ለዚህ ቃል ትክክለኛ ትርጒም ለመስጠት ዐውዱን መገንዘብ ነው። ዐውዱ ብቻ ትክክለኛውን ትረጒም ይወስናል።

በተመሳሳይ መንገድ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ በሆኑ ቃላትና ሐረጋት ይጠቀማል፤ ነገር ግን ትርጉማቸው ምን እንደ ሆነ የሚወስነው ዐውዱ ነው። «ሥጋ» እና «መንፈስ» የተሰኙ ቃላት ትርጉማቸው የሚለዋወጥበት ምክንያትም ይኸው ነው። በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ «ሥጋ» የሚያመለክተው አካልን ነው፤ (ፊል. 1፥24)። በሌላ ስፍራ ደግሞ ኀጢአተኛ ስለሆነው ስለ ሰው ተፈጥሮ የሚገልጽ ሆኖ ገብቷል፤ (ሮሜ 8፥12-13)። «መንፈስ» የሚለው በዐይን የማይታይ ርኩስ መንፈስን ሲያመለክት (ማር. 7፥25)፥ ሰብአዊ መንፈስን ደግሞ ያመለክታል፤ (2ቆር. 7፥1) እንደዚሁም መንፈስ ቅዱስን ሲያመለክት ይችላል፤ (ገላ. 5፥25)። የእነዚህ ልዩነቶች ትርጉም ግልጽ የሚሆንበት ጊዜ ቢኖርም ሌላ ጊዜ ደግሞ ግልጽ አይሆንም። አንድ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ወይም በሌላ ተመሳሳይ የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ በተደጋጋሚ ቢያጋጥመን የዚህ ቃል ትርጉም ሁልጊዜ አንድ ዐይነት ነው ብለን መገመት አንችልም። እዚህ ላይ ደኅና አድርገን መመልከት ያለብን ጸሐፊው ቃሉን የተጠቀመበትን መንገድ ነው።

«ኀጢአተኛ» የሚለው ቃል በተለያየ ትርጉም መገኘቱ ለዚህ ምሳሌ ሊሆን ይችላል። ምናልባት «ኀጢአተኛ» የተሰኘው ቃል ግልጽና ቀላል ስለ ሆነ፥ ትርጉሙ ሁልጊዜ ተመሳሳይ ነው ብለን እንገምት ይሆናል። ሰፋ አድርገን ስናስብ ይህ አስተሳሰብ እውነት ነው፤ ነገር ግን ልዩ ትርጉሙ በአገባቡና በአጠቃቀሙ ሁኔታ ሊታይ ይችላል።

የመክብብ ጸሐፊ «ኀጢአተኛ» በሚለው ቃል ሲጠቀም በአጠቃላይ በሰው ልጆች ላይ ያነጣጠረ ሳይሆን፥ በተለይ ቃሉን የተጠቀመው ኑሮ ሳይቃናላቸው ቀርተው ለተከፉና በጥበብ፥ በደስታና በሥራ አማካይነት ለሕይወታቸው ትርጉም ለማግኘት ለሚጥሩ ሰዎች ነው። «ኀጢአተኛው» እግዚአብሔርን ደስ ለሚያሰኘው ሰው ተቃራኒ ነው፤ (መክ. 2፥2 ፤ 7፥26)። ይህ ቃል በወንጌላት ውስጥ የተለየ ትርጉም አለው። በኢየሱስ ጊዜ «ኀጢአተኛ» የሚለው ቃል ልማዳዊ ትርጉሙ የሕግ ሰዎችን፥ ዘሙት አዳሪዎችንና ግብር ሰብሳቢዎችን የሚያመለክት ነው፤ (ሉቃ. 7፥34 ፥ 37)። ጳወሎስ ስለ ኀጢአተኞች የሚናገረውን ስንመለከት፥ አባባሉ ስለ ዓለም አቀፋዊው ነገረ መለኮታዊ ይዘት ሆኖ እናገኘዋለን፤ ክርስቲያኖችም ቃሉን የሚያዛምዱት ከዚሁ ፍቺ ጋር ነው፤ (ሮሜ 3፥23 ፤ 5፥8)።

ብዙ ጊዜ ቃላት ለዓመታት ሲቆዩ ትርጉማቸው ይለወጣል። እኛ ዛሬ በዘመናችን ትርጉማቸው ስለተለወጡ የተለያዩ ቃላት ማሰብ እንችላለን፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመንም ተመሳሳይ ሁኔታዎች ተፈጽመዋል። የመጽሐፍ ቅዱስን ቃላት መገንዘብ ያለብን፥ በዚያን ጊዜ ጸሐፊዎቹ ከጻፉበት ትርጉምና ይዘት በመነሣት እንጂ ከዛሬው ትርጉም አኳያ መሆን የለበትም።

እኛ ዛሬ ስለ «ነቢይ» ሲነግ፥ «ነቢይ» የሚባለው ስለ ክስተቶች (ለምሳሌ ስለ አየር ጠባይ የሚተነብይ) ሰው ይመስለን ይሆናል፤ ነገር ግን በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩ ሰዎች ስለ ነቢይ ያስቡ የነበሩት፥ እንደ መልእክተኛ ወይም እንደ ቃል አቀባይ አድርገው ነበር። አሮን ሙሴን ወክሎ በእርሱ ፈንታ ይናገር ስለ ነበረ ነቢይ ተብሎ ይጠራ ነበር፤ (ዘፀ. 7፥1)። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጽሑፎቻቸውን የምናገኘው ነቢያት እግዚአብሔርን ወክለው ትንቢት ይናገሩ ነበር። የታዘዙትን የእግዚአብሔርን ቃል ችላ ቢሉ ምን ሊከተላቸው እንደሚችልም ተንብየዋል። ያም ሆነ ይህ በዋናነት የእግዚአብሔር መልእክተኞች እንደ ነበሩ እንገነዘባለን። እነርሱ በመለኮት የተመረጡ፥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለሕዝቡ የሚያውጁ፥ ሰባክያን ነበሩ፤ (ኤር. 1፥7 ፤ 7፥2 ፤ 2፥1-2)።

## ሥዕላዊ ቋንቋ

ሌላው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቋንቋ የፈሊጣዊ አባባሎችና አጠቃቀም ጉዳይ ነው። በማንኛውም ንግግር ወይም ሥነ ጽሑፍ ውስጥ እንደምንመለከተው ሁሉ፥ መጽሐፍ ቅዱስም በውስጡ ዘይቤያዊ አባባሎችን በተደጋጋሚ ይጠቀማል፤ እኛም እነዚህን ዘይቤያዊ አጻጻፎች በምናገኝበት ጊዜ ቃል በቃል እንዳንተረጉማቸው መጠንቀቅ አለብን። ለምሳሌ «ዐይኑን አንሥቶ ተመለከተና አየ» የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አገላለጽ ቃል በቃል መተርጐም የለብንም። ነቢዩ አሞጽ ስለ አንዱና ስለ ሌላው ነገር አከታትሎ፥ እግዚአብሔር «ስለ ሦስቱ ኀጢአት፥ ይልቁንም ስለ አራቱ ቍጣዬን አልመልስም» ሲል፥ ሐሳቡ እያንዳንዱ አገር በሦስት ወይም በአራት ተለይተው በታወቁ ኀጢአተኞች ምክንያት ተቀጥቷል ማለቱ አይደለም። ነቢዩ በዚህ የአገላለጽ ዘይቤ መናገር የፈለገው፥ ደጋግመው ኀጢአት ሠርተዋልና ስለዚህም አሁን ከፍርድ አያመልጡም ለማለት ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ለማስተላለፍ የሚፈልጉትን ነገር አጕልተው ለመግለጽ ሲሹ በቍጥር አስደግፈው ይጽፋሉ። ለምሳሌ ነቢዩ ሚክያስ «ዐሥር ሺህ የዘይት ፈሳሽ» (ሚክ. 6፥7) ይላል፤ ሐዋርያው ጳውሎስ ደግሞ «ዐሥር ሺህ ቃላት በልሳን» ብሏል፤ (1ቆሮ. 14፥19)። በእነዚህ ምሳሌዎች እንደምንገነዘበው፥ መጽሐፍ ቅዱስ ቍጥሮችን እንደ ሒሳባዊ ቀመር ወይም ተመን አድርገን እንድናነብ አይፈልግም። አነጋገሩ ዘይቤያዊ ወይም በቀላሉ ግምታዊ የአገላለጽ ዘዴ ሊሆን ይችላል። ይህም «በብዙ መቶዎች»፥ «በደርዘኖች» ፥ «በብዛት» እንደማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ «አርባ» ቍጥርን ሲጠቅስ፥ ይህ ቍጥር ልክ እኛም እንደምናደርገው ዙሪያ ጥምጥምና ወይም ግምታዊ ነገርን የሚጠቁም ነው። አንዳንድ ጊዜ ቍጥሩ የቆመለት ወይም የሚያመለክተው መጠን ትክክል ሊሆን ሲችል፥ በሌላ ጊዜ ደግሞ ግምታዊ አቀራረብ ይሆናል።

አንድ ነገር ቃል በቃል የተነገረ ወይም የተተረጐመ አይደለም ስንል ይህ ነገር እውነት አይደለም ማለታችን አይደለም። አንድ ጊዜ በራእይ መጽሐፍ ላይ ስሰብክ ሳለሁ፥ ይህን መጽሐፍ ቃል በቃል መተርጐም አይገባም ብዬ ተናግሬ ነበር። ከሚያዳምጡኝ ሰዎች መካከል አንዱ፥ እኔ የመጽሐፉን ትክክለኛነት ያልተቀበልሁ መስሎት አባባሌን ተቃወመ፤ የእኔ ገለጻ ግን፥ እግዚአብሔር በራእዮች አማካይነት እውነቱን ገልጿል፤ እነዚህ ራእዮችም መተርጐም አለባቸው የሚል ነበር። ለምሳሌ የሰው ልጆች በዚህ ምድር ላይ ሳሉ አራት እግሮች፥ ሰባት ራሶች፥ ዐሥር ቀንዶችና ረጅም ጅራት ባለው እንስሳ ይተዳደራሉ ብዬ አላምንም። በራእይ ውስጥ የተጠቀሰው እንስሳ በተምሳሌትነት የተወከለ እንጂ ቃል በቃል ሊተረጐም አይገባም። ይህ በተምሳሌትነት የቀረበው እንስሳ የሰው ልጆችን እንዲያስተዳድር በሰይጣን የሚሾም ሰውን ይመስላል፤ ምልክትነቱም ለዚያ ይቆማል። ተምሳሌትነቱ አንድን እጅግ አስፈሪ፥ ገዳይና አጥፊ የሆነን ሰው፥ ነገር ወክሎ ቀርቧል እንጂ ልክ እንደ አንበሳ ወይም እንደ ድብ ያለ እንስሳን ይወክላል ማለት አይደለም።

የመጽሐፍ ቅዱስ ማጥኛ መጻሕፍትን ስናነብም ሆነ ሰባክያንን ስናዳምጥ በአንድ ወይም በሌላ ሁኔታ «ቃል በቃል» (በቁሙ) የሚለውን አገላለጽ ልንሰማ እንችላለን። ስለዚህ ጸሐፍያንም ሆኑ ተናጋሪዎች በዚህ ቃል አማካይነት ምን ማለት እንደ ፈለጉ ማስተዋል ይገባናል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ዘይቤያዊ አገላለጽ የተለመደ ነው፤ የተለመደ ሆኖ ካገኘነውም እንደ ቃሉ አገባብ ልንፈታው፥ ልንተረጉመው ይገባል። ቃል በቃል አንተረጉመውም ስንልም፥ አናምንበትም ማለት አይደለም። ጸሐፊው የጻፈውን እንቀበላለን፤ ምን ማለቱ እንደሆነም መገንዘብ እንፈልጋለን።

የብሉይ ኪዳን ነቢያት በእስራኤል ሕዝብ ውስጥ «እያንዳንዱ ሰው በገዛ ወይኑ ሥር፥ ከገዛ በለሱም ሥር ተቀምጦ» ያዩበት ወይም የተመለከቱበት ዘመን ነበር፤ (ሚክ. 4፥4)። ይህን ትንቢታዊ አባባል ቃል በቃል ብንፈታው ወይም ብንተረጉመው በእሥራኤል ሀገር ውስጥ ያለ ፥ እያንዳንዱ ሰው ሁሉ የወይንና የበለስ ዛፍ በየደጁ ተክሎ በማሳደግ፥ ያ የወይንና የበለስ ዛፍ ሲያድግ ሁሉም ሰው ከየቤቱ እየወጣ በወይኑና በበለሱ ዛፍ ሥር ይቀመጥ እንደማለት ይሆናል። ነገር ግን አጻጻፉ ግጥማዊ ይዘት ወይም ቅኔያዊ ምሥጢር አለው፥ ስለሆነም በቅኔያዊው ምሥጢር ብንፈታው ወይም ብንተረጉመው እስራኤላውያን ከማንኛውም አገዛዝ፥ ስቃይና ጭቁና ነጻ ሆነው በሰላምና በእርካታ፥ በገዛ ንብረታቸው ላይ ተዝናንተው የሚኖሩበት ተስፋ ወደ ፍጻሜ ይመጣል የሚል ትርጉም ይይዛል። ይህን አባባል የተረጐምነው ጸሐፊው በፈለገው መንገድ ነው።

## ብዙ መጻሕፍት ግን አንድ መጽሐፍ

በመጀመሪያ ደረጃ እያንዳንዱን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፥ እንደ ዐውደ ንባቡ መተርጐም እንዳለብን በዚህ ጥናት ውስጥ ተመልክተናል። እያንዳንዱ ጸሓፊ መልእክቱን ለአንባቢዎች ለማቅረብ የየራሱ የሆነ ዓላማ ስላለው፥ ጽሑፉንም መተርጐም ያለብን ከዚያው ዓላማ ተነሥተን ነው።

ያም ሆኖ፥ ማንኛውንም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፥ ከሌላው ጋር ሳናስተያይ እንተረጉመዋለን ማለት አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ሙሉነት ያለው መጽሐፍ ነው። ስለዚህ እያንዳንዱን መጽሐፍ በምናነብበት ጊዜ፥ ከጠቅላላው መጽሐፍ ቅዱስ ዐውድ አንጻር መሆን አለበት። ክፍሎቹን በምንመለከትበት ጊዜም ስለ መላው መጽሐፍ ቅዱስ የተሻለ መረዳት ይኖረናል፤ ስለ መላው መጽሐፍ ቅዱስ ስናስብም ስለ ክፍሎቹ የተሻለ ግንዛቤ እናገኛለን። ምንጊዜም ቢሆን እነዚህ ሁለት ነገሮች በሐሳባችን ውስጥ መኖር አለባቸው።

መጽሐፍ ቅዱስ አንድ መጽሐፍ ነው ብንልም፥ በእያንዳንዱ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኝ ቃል ሁልጊዜ አንድ ዐይነት ትርጒም አለው ማለት አይደለም። የዚህ ትክክለኛ ትርጒም በመጻሕፍቱ ስምምነትና ከስሕተት ነጻ በሆነ አጠቃላይ ራእይ ይገለጣል። እግዚአብሔር ከጊዜ ወደ ጊዜ መንገዱን ይለውጥ፥ ዕቅዶቹንም ይከልስ ይመስል መጽሐፍ ቅዱስን መቈራረጥና መሸንሸን የለብንም፤ መጽሐፍ ቅዱስ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው መለዋወጥ ሳይታይበት ራሱን ጠብቆ ይዘልቃል፤ እግዚአብሔር በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ የሚሠራቸውን ተግባራት ይዘግባል፤ ይህም በዔድን ገነት ከተፈጸመው ዐመፅ አንሥቶ በክርስቶስ እስከ ተፈጸመው የድነት ዕቅድ ድረስ ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ዕድገት ያለውን የድነት ዕቅድ የሚያስታውቅበት መንገድ «ርምደታዊ መገለጥ» ተብሎ ይጠራል። እግዚአብሔር በዚህ ሂደት የሚፈጽመው ተግባር በተለምዶ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርተ መለኮት ይባላል።

## መገለጥ ደረጃ በደረጃ

እግዚአብሔር ለሰው ዘር ታሪክ ትርጒም የሚሰጥ ዓላማ አለው፤ ይሁን እንጂ ይህን ዓላማውን በሰው ልጆች ታሪክ መጀመሪያ ላይ በአንድ ጊዜ አላሳወቀም። ሰዎችን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ለሚመጣው ሙሉ መገለጥ እያዘጋጃቸው በነበረው ሂደት፥ ደረጃ በደረጃ ገለጠው።

ሰዎች ከኀጢአት ምሕረትን፥ ይቅርታን በሚለምኑበት ጊዜ፥ የየትኛውም ዘር ወይም ዘመን ሰዎች ቢሆኑም ከእግዚአብሔር ፍጹም ምሕረትን ያገኛሉ። ሆኖም የእግዚአብሔር ይቅርታ ዘፈቀዳዊ፥ ድነቱም ነሲባዊ አይደለም። እንደ ፈቃዱ ይሠራል፤ መጽሐፍ ቅዱስም ይህ ዕቅድ እንዴት እንደሚያድግ ያሳያል።

ባጭሩ የእግዚአብሔር ዕቅድ አንድን ሰው (አብርሃምን) መምረጥ፥ ከእርሱም አንድን ሕዝብ (እስራኤልን) መፍጠር፥ ከዚህም ሕዝብ የዓለምን መድኀኒት፥ ኢየሱስን ማምጣት ነበር። የቀድሞዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች፥ እግዚአብሔር ሊመላለሱበት የሚገባቸውን ሥነ ምግባር (ሕገ ሙሴን)፥ ሊኖሩበት ያለውን ምድር (ከነዓንን) እንዴት ለእስራኤላውያን እንደ ሰጣቸው ይነግሩናል። ታሪኩ ሲቀጥልም እግዚአብሔር በእስራኤል መንግሥት ውስጥ የመሚሑ የኢየሱስ መምጫ የሆነውን (የዳዊትን ሥርወ መንግሥት) እንዴት እንዳቋቋመ ያሳያል። አዲስ ኪዳን በበኩሉ ኢየሱስ እንዴት አዳኝ ሆኖ እንደ መጣ፥ ቀጥሎም ተከታዮቹ የአዳኝነቱን መልእክት እንዴት ለዓለም እንዳዳረሱ ያብራራልናል። ይህ ድነትም በመጨረሻው ዘመን፥ ኢየሱስ ዳግም ሲመለስ ከፍጻሜ ይደርሳል።

አንድ ቀን የእግዚአብሔርን አጠቃላይ ዓላማዎችና የታሪክ አቅጣጫ ስንመለከት፣ መጽሐፍ ቅዱስን በተሻለ ሁኔታ እንገነዘባለን። ልዩ ልዩ መጻሕፍት ከእግዚአብሔር መገለጥ ጋር እንዴት ሊስማሙ እንደሚችሉ ስናውቅ፣ ያኔ በተሻለ ሁኔታ እንደምንተረጉማቸው ይገባናል። እያንዳንዱን መጽሐፍ ከተጻፈበት ዘመን አኳያ ማንበብ እንጂ፣ ጸሐፊው ከተናገረው በላይ መናገር የለብንም።

በዚህ መንገድ ከሁለት ስሕተቶች እንቈጠባለን። አንደኛው ስሕተት መጽሐፍ ቅዱስን የታሪክ መጽሐፍ ብቻ አድርጎ በመመልከት በቤተ መዘክር ውስጥ ካለ አንድ ተራ ሥነ ጽሑፍ እንደማይሻል መቊጠር ሲሆን፥ ሌላው ስሕተት ደግሞ ለእያንዳንዱ ክርስቲያናዊ የሆነ ዝርዝር ትርጉም ለመስጠት በመሞከር ሰው ሠራሽ መንፈሳዊነትን መፍጠር ነው። የሆነ ሆኖ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች የቀድሞዎቹ ጸሐፊዎች ካደረጉት የበለጠ በብሉይ ኪዳን ላይ ትኩረት የነበራቸው መሆኑ እውነት ነው፣ (1 ጴጥ. 1፥10-12)። ስለዚህ አዲስ ኪዳን ብሉይ ኪዳንን በምን አኳኋን እንደፈጸመ ማስተዋል ይገባናል።

## ወደ ፍጻሜ ማምጣት

እግዚአብሔር ዓላማዎቹን በቀጣይነት እንደ ገለጠ፥ እያንዳንዱ መገለጥም በፊተኛው ላይ የተደገፈ እንደሆነና በተመሳሳይ ጊዜ እንዳሳደገው አይተናል። የእያንዳንዱን የመገለጥ ደረጃ ትርጉም የምንገነዘበው አስቀድመው በተቀበሉት ሰዎች ግንዛቤ መጠን ነው። ሌሎች መገለጦች በተሰጡ ቊጥር የቀድሞው አይለወጥም፣ ሆኖም የላቀ ትርጉም ይኖረዋል። ብሉይ ኪዳንን የምንገነዘበው ባለበት ሁኔታ ነው፣ ስለ አዲስ ኪዳን ባለን ዕውቀት ደግሞ አሮጌውን በአዲሱ ብርሃን ውስጥ እናየዋለን። የክርስትና ዕውቀታችን የብሉይ ኪዳንን ትርጉም አይለውጠውም፣ ነገር ግን አዲስ ትርጉም ይሰጣል።

ብሉይ ኪዳን ዝቅተኛ ወይም ደረጃው የበታች ነው የሚል አስተያየት አለ፤ አዲስ ኪዳንን ግን ይህን የተዛባ አስተሳሰብ ያርመዋል:: አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር የብሉይ ኪዳንን ሥርዐት በተመለከተ ጥሩ ሥራ አልሠራም፤ ኢየሱስ በመጣ ጊዜ ግን እንደ ገና ሞክረና ሁሉንም ነገር ትክክል አደረገው ይላሉ:: ምንም እንኳን ብዙ ሰዎች ስለ ብሉይ ኪዳን መልካም አስተሳሰብ ባይኖራቸውና ቢያናንቁትም ክርስቲያኖች ግን ድፍረት ባለበትና ከሥነ ሥርዐት ውጪ በሆነ መንገድ ነቀፋቸውን አይገልጹትም:: ቅዱሳት መጻሕፍት በመንፈስ ምሪት የተጻፉና ሥልጣን ያላቸው መሆናቸውን የሚገልጹ ጥቅሶችን ከአዲስ ኪዳን ውስጥ ስንጠቅስ ፥ «ቅዱሳት መጻሕፍት» የሚለው አገላለጽ ብሉይ ኪዳንን የሚያመለክት ነው:: ብሉይ ኪዳን ወደ ድነት ሊመራን፥ የእግዘአብሔርን እውነት ሊያስተምረን፥ በመልካም ጠባይ ሊያሰለጥነንና ትርጒም ያለው ሕይወት እንድንኖር ሊያዘጋጀን ብቃት አለው፤ (2ጢሞ. 3፥15-17 ፥ ማቴ. 22፥29)::

ብሉይ ኪዳን ሙሉ ባለመሆኑ ብቻ እንደ ጒደሎ ይቈጠራል እንጂ፣ በትምህርቱ ወይም በአስተምህሮው ጒደሎ ነው በሚያሰኝ ነቀፋ ዐይነት ይህ ስም ሊወጣለት አይገባም:: አዲስ ኪዳን ብሉይ ኪዳንን ወደ ሙሉነት፥ ፍጹምነት፥ ያመጣዋል፤ ከፍጻሜም ያደርሰዋል እንጂ አያርመውም:: በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን መካከል ስምምነት አለ:: እግዚአብሔር የማዳን ዕቅዱን ለማሳወቅና ከፍጻሜ ለማድረስ የሚያደርገው ተግባር፣ ሳይቋረጥ ወይም ሳይለወጥ የሚቀጥል ነበር:: አዲሱ ዘመን በኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜም፣ እግዚአብሔር ጥንት አስቀድሞ የተናገረውን ወይም የሠራውን ሥራ ማረም አላስፈለገውም::

ይህን እውነታ ግልጽ ለማድረግ እስቲ አንድ ጊዜ ቤት ስለ መሥራት ሁኔታ እናስብ:: ገንቢው (ፕላን) ንድፍ ሠራ:: በመጀመሪያ የቤቱን መሠረት ይጥላል፤ ከዚያም ግድግዳዎቹን ያቆማል፣ ይቀጥልና ግድግዳና ጣሪያውን ያስተሳሥራል:: ልክ እንደ ብሉይ ኪዳኑ መገለጥ ቤቱ በዚህ ደረጃ ላይ ገና ያልተደመደመና ያልተፈጸመ ቤት ነው፤ ይሁን እንጂ ባለበት ሁኔታ ምንም የሚያስከፋ ነገር የለበትም:: እያንዳንዱ የቤቱ ክፍሎች በትክክል ተሠርተዋል:: ስለዚህ ዓላማው ሠምሯል፤ የግንባታው ሥራም ወደ ፊት ይቀጥልና ቤቱ ከፍጻሜ ይደርሳል:: ቤቱን የሚሠራው ሰው ገና ከመጀመሪያው በግንባታ ላይ እያለ ምንም ነገር አያፈርስም:: ሥራውን ይቀጥልና ከፍጻሜ ያደርሰዋል:: ይህም እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል እንዳደረገውና እንዲሁም በአዲስ ኪዳን መገለጥ ላይ እንዳከናወነው ማለት ነው::

ይህ ሁኔታ፥ የአዲስ ኪዳን ጸሓፊዎች ብሉይ ኪዳን በአዲስ ኪዳን ውስጥ ፍጻሜ ስለ ማግኘት ጒዳይ ሲጽፉ ምን ማለታቸው እንደ ሆነ ነገሩን እንድንገነዘብ ይረዳናል:: ለእነርሱ ከፍጻሜ መድረስ ማለት፣ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች እውነት ሆኑ ማለት ብቻ ሳይሆን፥ አባቶቻቸው ስለወደፊቱ ሁኔታ ትንቢት በመናገር ረገድ ምን ያህል ችሎታ እንደ ነበራቸው ማሳየትንም እንደ ተግባራቸው ቈጥረውት፥

እግዚአብሔር በእስራኤል ታሪክ አማካይነት ለሰው ልጆች ይሠራ የነበረውን የዕቅድ መፈጸም ተመልክተውት ነበር:: አሁን ዕቅዱ በኢየሱስ አማካይነት ከፍጻሜ ደርሷል፤ ይህንንም የቀድሞ ሰዎች ሊያረጋግጡት ባልቻሉት በብሉይ ኪዳን መገለጫዎችና ክስተቶች፥ በተለየ ሁኔታ እውነቱን ሊመለከቱ ችለዋል፤ (ለምሳሌ :- ማቴ. 4፥14-16 ፤ 12፥17-21)::

ይህን ሐሳብ ፀተጨባጭ ምሳሌ ለመግለጽ፥ ቀደም ሲል ወደ አነሣነው ወደ ቤቱ ግንባታ ሁኔታ እንመለስ:: ቤተ ሠሪው በፕላኑ (በንድፉ) ላይ እንደተመለከተው አንድ ባለ አራት ካሬ ሜትር ክፍል ለመሥራት ባለው ዕቅድ መሠረት፥ ክፍሉን ለመሥራት ግድግዳዎቹን አቆመ:: የሚያደርገውን ያውቅ ነበርና ሥራውን በትክክል አከናወነ:: አሁን ቤቱ አልቋል፤ የቤቱ ባለቤት የሠራው ምሥጢራዊ ዕቅድም አራት ካሬ ማትር የሸፈነ ክፍል ሠርቶ ወደዚያ መግባት እንደ ነበረ አውቀናል:: ግንበኛው ቤቱን በሚሠራበት ጊዜ ወለሉ ምን ያህል ካሬ ሜትር እንደሚሸፍን አያውቅም ነበር:: የቤቱ ባለቤት ግን ይህን ያወቅ ስለ ነበር የክፍሉን ስፋት አራት ሜትር አደረገው:: የብሉይ ኪዳን ጸሐፊዎች በሚጽፉበት ጊዜ በወቅቱ የራሱ ትርጉም ነበረው:: የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች እግዚአብሔር እንዴት ይሠራ እንደ ነበረ ባረጋገጡ ጊዜ ግን የበለጠ ትኩረት፥ የበለጠ ስፍራ አገኘ:: በዕቅዱ እግዚአብሔር አስቀድሞ ባቀደው መሠረት ይሠራ ነበር፤ አሁን ደግሞ ዕቅዶቹን በኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ፍጻሜ አደረሰ::

አዲስ ኪዳን ብሉይ ኪዳንን ከፍጻሜ የሚያደርስ ሲሆን፥ እኛም ብሉይ ኪዳንን በበለጠ በምንገነዘብበት ጊዜ፥ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የበለጠ ትርጉም እናገኛ ለን፤ በተመሳሳይ ሁኔታ ስለ አዲስ ኪዳን የተሻለ ግንዛቤ በሚኖረን ጊዜ፥ በብሉይ ኪዳን ውስጥ የበለጠ ትርጉም እናገኛለን:: ቀጣይነት ያለው የእግዚአብሔር መገለጥም በከፍተኛ ደረጃ የሚገኘው በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሲሆን፥ በተለይም በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ነው:: በእርሱ ምክንያት በአዲሱ ብርሃን ውስጥ የምንመለከተው ብሉይ ኪዳንን ብቻ ሳይሆን፥ መላውን የአዲስ ኪዳን ታሪክ ጭምር የሚያካትት ነው::

## ፬

## ሌሎችን መርዳት

### የመተማመን መሠረት

መጽሐፍ ቅዱስን በመተርጐም ረገድ አንድ ጊዜ ትክክለኛውን መንገድ ተከትለን ካዳበርነው፥ የምናቀርበውን ስብከትና ትምህርት የምንገነባበትን መሠረት ጣልን ማለት ነው:: በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚያሳስበን ጉዳይ ስለ ጠቅላላው የስብከት ዘዴ ሳይሆን፥ እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን በሰጠበት ሁኔታ ሰዎች እንዲገነዘቡት ከመርዳቱ ላይ ነው:: እኛ ራሳችንም እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን በሰጠበት መንገድ ካልተገነዘብነው በስተቀር ይህን ማድረግ አንችልም::

ክርስቲያኖች ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመስበክ ጸጋ የላቸውም፤ ደግሞም ሰባክያን የሆኑ ሁሉ ስጦታዎቻቸውን በሚገባ አይጠቀሙባቸውም:: ስብከቶቻቸው ይበልጥ ተቀባይነት እንዲያገኙላቸው ሲሉ በተለያዩ ዘዴዎች ይጠቀሙ ይሆናል:: ብዙዎቹ ወደዚህ ውስብስብ ሁኔታ ሲገቡ የመጽሐፍ ቅዱሱን ሐሳብ ይቀንሳሉ:: ዛሬ ትልቅ ሚና ባላቸው በውይይቶች፥ በቃለ መጠይቆች፥ በጥያቄዎች፥ በድራማዎችና በፊልሞች የሚታየውን ተግዳሮት ሲመለከቱ የስብከትን ፋይዳ እስከ መጠራጠር ይደርሳሉ:: በኅብረተሰብ ውስጥ የሚኖረው ለውጥ ምንም ይሁን ምን፥ የተሳካ ስብከት ሁልጊዜ ፋይዳ አለው፤ ሥልጣንም አለው:: ቤተ ክርስቲያን የፈለገችውን ያህል በሌሎች የመገናኛ ዐይነቶች ብትጠቀም የተሳካ መርሐ ስብከት ለቤተ ክርስቲያን ሕይወት አስፈላጊ ነው::

### መስበክና ማስተማር

መጽሐፍ ቅዱስን በተሻለ ሁኔታ ስለ መግለጥ ስናስብ በስብከትና በማስተማር መካከል የጐላ ልዩነት ለማድረግ እንሞክር:: ምክንያቱም ሁለቱም ተግባራት፥ መስበክና ማስተማር በጣም የተዛመዱ ከመሆናቸው የተነሣ በመካከላቸው የሚታየው ልዩነት ጥቂት ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተመዘገቡት ምሳሌዎች መካከል አንድ ሰው ሰባኪም፥ አስተማሪም ሆኖ እናገኘዋለን፤ (ማቴ. 4÷23 ፤ ሐዋ. 15÷35 ፤ 2ጢሞ. 4÷2)::

የመጽሐፍ ቅዱስ ምሳሌዎች እንደሚያሳዩት የመስበክና የማስተማር ተግባራት ሰፊ የሆኑ ሥራዎችን ይሸፍናሉ፤ አልፎ አልፎም አንዱ ሌላውን ሲተካው እንመለከታለን:: ስብከት የሚያተኩረው በተለይም የእግዚአብሔር ምሕረት ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች የምሥራቹን ቃል በማወጅ ተግባር ላይ ነው፤ (ሉቃ. 4÷18፤ ሐዋ. 8÷4 ፤ 12÷40 ፤ 1ተሰ. 2÷9):: በአንጻሩ የማስተማር ተግባር ትኩረት የሚያደርገው በክርስቲያናዊ እውነትና ባሕርይ ላይ ነው፤ (ሐዋ. 20÷20፤

1ቆሮ. 4÷17 ፤ ቲላ. 2÷7)፡፡ የማስተማሩ ሥራ ግን ላለመኑ ሰዎችም አስፈላጊ ነው፤ (ሉቃ. 4÷31-32፤ ሐዋ. 4÷2፤ 2ጢሞ. 2÷24-26)፡፡ የወንጌልን ትልልቅ እውነቶች መሰበክም እጅግ አስፈላጊ ነው፤ (ሮሜ 1÷15-16 ፤ 16÷25)፡፡

በነዚህ ጥናቶች ውስጥ፥ በስብከትና በማስተማር መካከል የጉላ ልዩነት ማድረግ እንደሌለብን እንገነዘባለን፡፡ አሁን ዋናው የሚያሳስበን ነገር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለ መስበክ እንጂ ስለ ወንጌል ስርጭት አይደለም፡፡ ያም ቢሆን ለዓለም የተሰጠው የእግዚአብሔር የተስፋ መልእክት እርሱን ማእከል ያደረገ ስለ ሆነ፥ ክርስቶስን መስበክ ማለት ወንጌልን መስበክ ማለት ነው፤ (2ቆሮ. 4÷5-6)፡፡

## የሰባኪው ሥልጣን ምንድን ነው?

እግዚአብሔር ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ስለ እርሱ እንዲማሩ፥ እርሱንም በግልጽ እንዲያውቁትና ለእነርሱ ባዘጋጀው ዕቅድ መሠረት በጥበብ እንዲሄዱ ይፈልጋል፡፡ ስለዚህም ራሱን ለዓለም ገለጠ፡፡ በብሉይ ኪዳን ዘመን በተለያዩ ሁኔታዎች ተናግሯል፤ በቅዱሳት መጻሕፍት አማካይነት ተናግሮ ነበር፤ ኢየሱስ ከመጣ በኋላ ግን አምላክ ሆኖ ሳለ ሰው በሆነ በእርሱ አማካይነት አስደናቂ በሆነ መንገድ ተናገረ፤ (ዮሐ. 1÷1÷14 ፤ ዕብ. 1÷1-2)፡፡ በማንኛውም ዘመን፥ በማንኛ ውም ሀገር የሚገኙ ሕዝቦች ሁሉ ስለ እርሱ በግልጥ እንዲማሩና በግል ሕይወታቸውም እንዲያውቁት፥ በዓለም ዙሪያ እንዲሠራጭ ስለ ራሱ የተጻፈ መገለጥን ሰጥቷል፤ (2ጢሞ. 3÷15-17 ፤ 2ጴጥ. 1÷20-21)፡፡

እግዚአብሔር ቅዱሳት መጻሕፍትን ለሕዝቦች በመስጠቱ፥ እኛ የመጽሐፍ ቅዱስ መምህራን በእግዚአብሔር ፊት ልዩ ኀላፊነት አለብን፡፡ ቃሉን አብራርተን በማስተማርና በተግባር ላይ እንዲውል በማድረግ ረገድ የእርሱ ወኪሎች ሆነን እናገለግላለን፡፡ እኛ የእግዚአብሔር፥ የመገለጡ ባለ ዐደራዎች ስለ ሆንን፥ ይህን በተግባር ላይ ለማዋል እጅግ መትጋት አለብን፡፡ ጳውሎስ ስለራሱና ስለ ባልደረቦቹ ሲናገር፥ በአእምሮው ውስጥ የነበረው የእግዚአብሔር እውነት ባለ ዐደራነት ነበር፡፡ አገልጋዮች ወይም መጋቢዎች የእግዚአብሔርን ቃል ተግባራዊ እንዲያደርጉት ዐደራ ስለተሰጣቸው ታማኞች ሊሆኑ ይገባል (1ቆሮ. 4÷1-2)፡፡ ሰባክያን ሁሉ በታማኝነት መንፈስ የእግዚአብሔርን ቃል ከእውነተኛ ትርጉሙ ጋር ለአድማጮቹ ሕይወት በሚበጅበት መንገድ ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በምንሰብክበት ጊዜ የራሳችን ያልሆነውን መልእክት የምንገልጥና የምናውጅ ሰዎች ነን፤ ይሁን እንጂ መልእክቱን እንደ መልእክታችን አድርገን ክብደት በመስጠት መተንተን ይገባናል፡፡ የሌላ ሰው መልእክት ከምናስተላልፍበት አኳኋን በላቀ መንገድ ማስተላለፍ አለብን፤ ይህን ስናደርግም በሕይወታችን ውስጥ ባገኘነው ተመክሮ ትግልም ይሁን አሸናፊነት አድማጮቻችንን እናስተምራለን፡፡

የሐዋርያው ጳውሎስን ፈለግ የምንከተል ከሆንን፥ የእግዚአብሔርን መልእክት በሙሉ እንናገራለን፤ አድማጮቻችንን የሚጠቅመውን ነገርም ሁሉ ወደ ኋላ አናስቀርም። ቃሉን እናስተምራለን፤ ነገር ግን ቃሉን በማስተማር ብርታትን ፥ ማስጠንቀቂያንና ማሳሰቢያን እንዲሁም በቃሉ ውስጥ የተካተቱ ኀለፊነቶችን እናሳውቃለን፤ (የሐ. 20፥20፥27)። ስብከት በምናቀርብበት ጊዜ የሆነ ሥልጣን ይሰማናል፤ ነገር ግን ሥልጣኑ የምናውጀው ቃል ሥልጣን ነው። የፈለግነውን ሁሉ የመናገር ሥልጣን የለንም፤ እንዲሁም ሰላማውያን በሆኑ ምእመናን ላይ የግል አስተያየታችንን ወይም እምነታችንን መጫንም አንችልም።

የብሉይ ኪዳን ነቢይ «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል» (አሞጽ 2፥4-6)፥ ኢየሱስም «እኔ ግን እላችኋለሁ» (ማቴ. 5፥27-28) ይላል። እኛ ግን ዛሬ ለራሳችን እወጃ መለኮታዊ ሥልጣን ስንሰጥ መጠንቀቅ አለብን። ልክ እንደ አድማጮቻችን እኛም በአንድ ሥልጣን ሥር ስለ ሆን በምናቀርበው ጥያቄ በምንጠቅሰው ችግር ውስጥ ራሳችንን ደምረን «እናንተ» በማለት ፈንታ «እኛ» ብለን ብናጠቃልለው መልካም ነው። «ወንጌልን ለጎረቤቶቻችሁ የማድረስ ኀላፊነት አለባችሁ» ከማለት ይልቅ «ወንጌልን ለጎረቤቶቻችን የማድረስ ኀላፊነት አለብን» ማለት የተሻለ ነው። ራሳችን በምናደርገው ተግሣፅና ምክር ከሌሎች በምንጠብቀው ድርጊትና ኀላፊነት ውስጥ ራሳችንን የማስገባት ልምድ ስናዳብር የበለጠ ትሕትናን እንላበሳለን፤ በሰው ላይ የምንሰነዝረው አጕል ፍርድም ይቀንሳል። የሰባኪው የሥልጣን ምንጭ ሁልጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ እንጂ፥ የመስበኪያው ስገነት አለመሆኑን እናስታውስ።

እንደ ሰባኪነታችን ሥልጣን ሊኖረን ይችላል፤ ሥልጣናችን ግን አምባገነናዊ ሊሆን አይገባውም። ከምንሰብከው ቃል የተነሣ በኀይልና በሙሉ ልብ ልንናገር እንችላለን፤ ነገር ግን አድማጮቻችን ለምንናገረው ሁሉ ያላንዳች ጥያቄ እንዲታዘዙ ማድረግ የለብንም። ለምንሰብከው ቃል መንፈሳዊ ምላሽ መጠበቅ መልካም ነው፤ ሰዎች የግል ሐሳባችንን እንዲቀበሉ ማስገደድ ግን አንችልም።

ደግሞም ከምእመኑ አንድ ዐይነት መልስ ወይም አስተያየት ለማግኘት ብለን ስሜታቸውን አላግባብ መንካትና ማስፈራራት የለብንም። ከዚህ ይልቅ የመጽሐፍ ቅዱስን ትርጕም በግልጽ በማብራራትና ተግባራዊ በማድረጉ ላይ ብናተኵር የተሻለ ነው። ይህን የመሰለ አሰባበክ መዝናናት ለሚፈልጉት አይጥምም ይሆናል፤ ሆኖም ለአብዛኞዎቹ ሰዎች መልካምና ዘላቂ ውጤት ይኖረዋል። ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡ ምእመናን መጽሐፍ ቅዱስን በበለጠ እንዲገነዘቡ የሚረዳቸውን ስብከት ይመርጣሉ።

### በመጀመሪያ ትርጕሙ፥ ከዚያም ተዛምዶው

መጽሐፍ ቅዱስን በማስተማር ረገድ ያለብን ኀላፊነት፥ የምናስተምረውን ክፍል ደኅና አድርገን መገንዘብ፥ ከዚያም ትርጕሙን ለአድማጮች ማስማት

ነው:: በተለምዶ አድማጮችን የሚመግብ ስብከት ማቅረብ እንሻለን፤ ሆኖም የምንሰብከው የመጽሐፍ ክፍል ከታሪኩና ከጭብጡ አኳያ ትርጉሙ ምን እንደ ሆነ ማብራራት ግዴታችን መሆኑን መዘንጋት የለብንም:: በተግባር ላይ የማዋሉ ሁኔታ ከጸሐፊው ዓላማ ጋር የሚስማማ ሊሆን ይገባል:: ለመናገር የምንፈልገውን ትተን፥ መጽሐፍ ቅዱስ መናገር የሚሻውን እንዲናገር ዕድሉን እንስጠው::

ሰዎች አንድ ጊዜ በሚገባ መጽሐፍ ቅዱስን ከተገነዘቡት፥ በራሳቸው ላይ ውጤታማ ሊሆን ያገኙታል:: የመጽሐፍ ቅዱስ አመጣጡ ጥንት ቢሆንም ዛሬም ሕያውና የሚሠራ ነው፤ (ዕብ. 4፥12):: መጽሐፍ ቅዱስ በየዘመናቱ በሰዎች ሕይወት ውስጥ ድንቅ የሆነ ሥራውን ይሠራል:: የሕያው እግዚአብሔር ቃል ዛሬም የሚናገር ስለ ሆነ በማንኛውም ትውልድ ውስጥ እውነቱን ገልጦ ማስተማር በሚችልበት መልኩ ያስተምራል እንጂ እያንዳንዱ ጥቅስ ለእያንዳንዱ ክርስቲያን ሕይወት የሚስማማ ልዩ መልእክት እንዲሆን አድርጎ አይናገርም::

ሆኖም ሰባኪው ሲሰብክ ተስፋ የሚያደርገውን ያህል የሚሰጠውንና የሚያብራራውን ትምህርት፥ ሰሚዎች ሁሉ ነቅተው ላያዳምጡት ይችላሉ፤ እነርሱም የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ምን ያህል ከሕይወታቸው ጋር ተያያዥነት እንዳለው ማስተዋል ይሳናቸዋል:: እንደዚሁም በምንሰብክበት ወቅት በፊታችን ያለውን የቅዱስ መጽሐፍ ቃል ማብራራት ብቻ ሳይሆን ይህ ቃል ለምእመኑ ሕይወት ምን ያህል እንደሚጠቅም ሐሳብ በማቅረብ ማገዝ ይገባናል:: ነገር ግን ያዘጋጀናቸው ትምህርቶች ምንም ያህል ለአድማጮቻችን ይጠቅማሉ ብለን ብናምንም እነዚህን ትምህርቶች እንዲቀበሉ ማስገደድ የለብንም:: መጽሐፍ ቅዱስ ማድረግ ስላለበት በመንገር ፈንታ ራሳችንን ለመጽሐፍ ቅዱስ ማስገዛት ይገባናል::

ትክክል የሆኑ የአሰባበክ ዘዴዎችን ከመሻት ይልቅ፥ ቅዱሳት መጻሕፍትን በትክክል መተርጐሙ የበለጠ አስፈላጊ ነው:: እንዲህ ስንልም የመርሐ ስብከትን አቀራረብ በተመለከተ ሊኖር የሚገባውን ሥልጠና ችላ እንላለን ማለት አይደለም:: አንድ ልናስታውሰው የሚገባ ቁም ነገር፥ ከሁሉም በላይ ለስብከታችን ፋይዳ የሚሰጠው ወይም ወሳኙ ነጥብ ይዘቱ ነው::

## መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉም እንዲያውቀው ይፋ ሆነ

በአይሁድ ምኩራብ ልምድ መሠረት የነበረው ሁኔታ፥ በመጀመሪያ ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብ፥ ከዚያም ቅዱሳት መጻሕፍቱን በሚያብራራና ለአድማጮቹ እንዲገባ በሚረዳ መንገድ መስበክ ነበር:: ይህ አሠራር አንዳንድ ጊዜ ገላጭ ስብከት ተብሎ ይጠቀሳል:: ይህ የስብከት ዘዴ አድማጮች ሙሉ ግንዛቤ ያገኙ ዘንድ መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ ሆኖ ተብራርቶ የሚቀርብበት መንገድ ነው:: በዚህም ሰሚው ትርጉሙን ይረዳል:: ይህ አካሄድ ኢየሱስ በናዝሬት በምኩራብ ውስጥ ካደረገው ጋርና (ሉቃ. 4፥16-21)፥ ሐዋርያው ጳውሎስ በአንጾኪያ

ከፈጸመው ተግባር ጋር ይመሳሰላል፣ (ሐዋ. 13፥14-16)። እነርሱም ሰዎች የቅዱሳት መጻሕፍትን ምሥጢራት ይገነዘቡ ዘንድ አብራርተውና አስፋፍተው ሰበኩ፣ ደግሞም አስተማሩ።

የቀድሞዪቱ ቤተ ክርስቲያን የምኩራቡን ሥርዐት ተከትላለች፣ ሆኖም በብሉይ ኪዳኑ ጽሑፍ ላይ የሐዋርያትን ጽሑፎች ትጨምር ነበር። የሐዋርያትን ትምህርቶች ልክ እንደቀሩት ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ ሥልጣን እላቸው ብላ ተቀብላ ነበር፣ (1ቆሮ. 14፥37 ፣ 1ተሰ. 5፥27 ፣ 2ጴጥ. 3፥15-16)። በጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን መርሐ ስብከት ውስጥ ቅዱሳት መጻሕፍትን ማብራራትና የክርስቲያንን እምነት ማስተማር፥ እንዲሁም በተግባር ላይ ማዋል ዋና ዋና ነገሮች ነበሩ፣ (2ተሰ. 2፥15 ፣ 1ጢሞ. 4፥13 ፣ 2ጢሞ. 2፥2፥15)። ዛሬም ይህ አካሄድ ሊጠቅም ይችላል። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስብከት አንድን መጽሐፍ ወይም የመጽሐፍ ክፍል፥ ወይም ርእሰ ጉዳይ ገላጭ ስብከት መሆን አለባቸው። አሠራሩ ይህን መንገድ በሚከተልበት ጊዜ ቅዱሳት መጻሕፍት በግልጽ እንዲታወቁ፥ ተብራርተው ለሰሚው እንዲቀርቡና ተቀባይነትም እንዲያገኙ ያግዛል።

ገላጭ መርሐ ስብከት ስንል (በተለይ የቅዱስ መጽሐፍን ክፍል በተመለከተ)፥ ክፍሉን ጥቅስ በጥቅስ ወይም ቃል በቃል ልክ የአንድምታ ወይም የትምህርት መጽሐፍ፥ ለአድማጮቻችን እንደምናነበው ዐይነት እንሄድበታለን ማለት አይደለም። አንድ ርእሰ ጉዳይን በተመለከተ፥ ለሐሳቦቻችን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ ለማግኘት አንድ የተመረጠ ጥቅስ እናነባለን ማለትም አይደለም። ዋናው መልእክታችን መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑን ለመግለጽ ነው። አብዛኛው የስብከት ጊዜ የሚያልቀው ቅዱሳት መጻሕፍቱን በማብራራትና በማስተማር ላይ ነው። ሰሚውን የሚመለከቱ ሐሳቦችን መናገር፥ ማስጠንቀቅ፥ መገሠጽና ማበረታታት ከፊሉን ጊዜ ይይዛሉ፣ ይህም የጊዜውን አነስተኛ ክፍል ይይዛል። ታድያ ኀይል ያለው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንጂ በሰባኪው ላይ አይደለም።

**ያለፈውን ከዛሬው ጋር ማዛመድ**

ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ለቀድሞዎቹ አንባብያን ምን ማለቱ እንደ ነበረ ማወቅ ይፈልጋሉ፣ በአንጻሩ እነርሱንም ምን ያህል እንደሚጠቅማቸው መረዳት ይሻሉ። ስለዚህ ስብከታችን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጭብጥ ጋር የሚስማማና የሚታመን የምእመናንን ዕለታዊ ሕይወትና ኑሮ የሚዳስስ መሆን አለበት።

በምንሰብክበት ጊዜ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የላቀ ግንዛቤ ሊኖረን ይገባል። ስለዛሬው ሕይወት ፍላጎቶች፥ ዝንባሌዎች፥ ችግሮችና እንዲሁም ስለ ሌሎች ጉዳዮች በቂና ተግባራዊ የሆነ ዕውቀት ሊኖረን ይገባል። ሰዎች እንዴት እንደሚያስቡና ምን እንደሚሰማቸው ማወቅና በተለመደ ቋንቋ ማነጋገር አለብን። ስብከት ሰዎች ከሚኖሩበት የገሃዱ ዓለም እውነታ ጋር የተዛመደ መሆን አለበት።

መጽሐፍ ቅዱስ ዛሬ ሰዎች በዓለም ላይ ለሚያጋጥሟቸው ነገሮች ሁሉ ቀርጥ ያለ መልስ አይሰጥም፤ የት መኖር እንዳለብን፥ ምን ዐይነት ሥራ እንደሚስማማን፥ ስንት ልጆች ሊኖሩን እንደሚገባ፥ ገንዘባችንን እንዴት ማስተዳደር እንደምንችል አይነግረንም:: በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን የነበሩ ሰዎች የሥራ፥ የጋብቻ፥ የቤተ ሰብ፥ የበሽታ፥ የድኽነት፥ ፍትሕን የማጣት፥ የፖለቲካ፥ የወንጀልና ሌሎችም ችግሮች ነበሩባቸው:: የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ስለነዚህ ችግሮች ብዙ ተናግረዋል:: ከቅዱሳት መጻሕፍት በመነሣት እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን የተናገረውን በምንገልጽበት ጊዜ ለዛሬው ኅብረተ ሰብ ትምህርትና መመሪያዎችን መስጠት እንችላለን::

የዚህ ዐይነት አሰባበክ መጽሐፍ ቅዱስን ከትርጕሙ ጋር ተስማሚና ተአማኒ ከማድረጉም በላይ ለዛሬው ጊዜ አስተዋጽኦ እንዲኖረው ያደርጋል:: እንደዚሁም ብዙ ስህተቶችን ያስወግዳል:: አንደኛው ስህተት የሚመጣው መጽሐፍ ቅዱስን እንደ አንድ ተራ የታሪክ ሰነድ አድርጎ ከማንበብ ሲሆን ይህ ተግባር ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስን ከማንኛውም ዓይነት ጥናታዊ ጽሑፍ አይለየውም:: ሌላው ስህተት ደግሞ ለማንኛውም ችግር ጥያቄ መልሱን ለማግኘት መጽሐፍ ቅዱስ ለመጀመሪያዎቹ አንባቢዎች ምን ማለቱ እንደ ሆነ አለመቀበል ነው:: ተጨማሪው ስህተት ደግሞ ስለ ዕለታዊ ሕይወት ያለውን እውነታ ችላ በማለት ስለ ክርስቲያንነትና ስለ መንፈሳዊ ሁኔታዎች ብቻ ማሰብ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ በተረጋገጠ ሁኔታ በችግሮች መካከል መንፈሳዊ ብርታትን ይሰጣል:: አሁን ካለንበት ኀላፊነት በመሸሽ ስለ ወደፊቱ ክብራችን እንድናስብ አያበረታታንም::

## የረጅም ጊዜ ዓላማዎች

በማብራሪያ የተደገፈ ትምህርት ሰዎች ስሕተቶችን እንዲያስወግዱ ከመርዳቱም በላይ ክርቲያናዊ አስተሳሰባቸውን እንዲያዳብሩ አዎንታዊ ጠቀሜታም አለው:: ክርስቲያኖች በዚህ ዓለም ላይ የተለያዩ ነገሮችን እንዴት ማስተናገድ እንዳለባቸው ማወቅ ይሻሉ:: በክርስቲያናዊ መንፈስ ማሰብ ሲለምዱ ይህንን ለማድረግ ብቃቱ ይኖራቸዋል:: የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀት የአስተሳሰብ መንገዳቸውን ይለውጣል፤ አዕምሯቸውን ያድሳል፤ በሚያጋጥሟቸው ሁኔታዎች ሁሉ የእግዚአብሔር ፈቃድ ለእነርሱ ምን እንደ ሆነ ያውቃሉ፤ (ሮሜ 12፥2)::

መጽሐፍ ቅዱስ ዘወትር በሚያጠኑት ሰዎች ውስጥ ባለማቋረጥ ይሠራል:: በዚህ ባሕርዩም ሕይወታቸውን በመለወጥ ይበልጥ እግዚአብሔርን እንዲመስሉና እርሱንም ደስ ለማሰኘት በውሳኔያቸው ላይ ተፅዕኖ እንዲኖራቸው ያደርጋል:: እንደ ሰባክያን ቅዱሳት መጻሕፍትን በማንበብና በማጥናት ይህን የለውጥ ሂደት መርዳት እንችላለን፤ በዚህም እግዚአብሔር በሰዎች ሥራ ውስጥ ስላለው ተግባር አድማጮች ሰፊ አድማስ እንዲኖራቸው እናደርጋለን::

አንዳንድ ጊዜ ሰዎች «ከዛሬው ሕይወታችን ጋር የተዛመደ፥ በዕለታዊ ሕይወታችን ውስጥ የሚረዳን ስብከት እንሻለን» ይላሉ:: ይህ ተገቢ የሆነ ፍላጎት ቢሆንም በውስጡ የተደበቀ አደጋ አለበት:: አሁን ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተዛመደ ስብከት ለማድረግ እናስብ ይሆናል:: ይህን ስናደርግ የሰዎችን ፍላጎት በሚያረካ ስብከት ላይ ስለምናተኩር ሁኔታው በምንሰብክበት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ላይ ብቻ ይወሰናል:: ይህ ድርጊትም አርቆ አለማሰብን ያሳያል፤ ምክንያቱም ክርስቲያኖች አሁን በፊታቸው ባሉት ፍላጎቶቻቸው ላይ ብቻ እንዲያነጣጥሩ ያደርጋቸዋል:: ይህም ለጤናማ ክርስቲያናዊ ሕይወት መዳበር ዕንቅፋት ይሆናል::

ለምሳሌ :- መጽሐፍ ቅዱስን በማነብበት ጊዜ አካላዊ ሥቃይን የሚመለከቱ ጉዳዮችን አገኘሁ ልበል፥ እነዚህም ሥቃዮች ሰዎች በምን ምክንያት ለሥቃይ እንደ ተዳረጉ፥ ስላሠቃዩአቸው ሰዎች ምን ማድረግ እንዳለባቸው፥ ለተአምራዊ ፈውስ ምን ዕድል እንዳላቸው የሚሉና ሌሎችንም አገኛለሁ:: እኔ ጤናማና ሁሉ_ነገር የተስማማኝ ሰው ስለ ሆንሁ እነዚህ ነገሮች በአሁኑ ጊዜ ከእኔ ሁኔታ ጋር ላይዛመዱ ይችላሉ:: በሕይወቴ፥ በሙሉ ስሜቴ ይኸው ሆኖ ቆይቷል:: በሰው ልጅ ላይ ያሉ ሥቃዮች ሁሉ ለእኔ በአብዛኛው ቃላዊ ናቸው::

ይሁንና ስለወደፊቱ ምንም አላውቅም:: በጤናዬ ላይ ለውጥ ሲታይ፥ አካለ ስንኩልነት ይደርስብኝ፥ በጣም የሚቀርበኝ ሰው ለሞት በሚያደርስ አደገኛ በሽታ ይለከፍ ይሆናል:: ለእኔ ጠቃሚ ያልመሰሉኝን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በመዝለሌ ምክንያት የተለያዩ ክስተቶች በሚያጋጥሙኝ ወቅት ለመቋቋም ዐቅም አይኖረኝም:: ትምህርት ከፍላጎት ጋር የተዛመደ መሆን አለበት የምለው ሁሉ አሁን አርቄ አለመመልከቴን እያጋለጠብኝ ነው:: ለእኔ መስማማት አለበት ብዬ ስወተውት የነበረበት ሁኔታ ራስ ወዳድነቴን ያሳያል:: የወደፊቱን ለመቋቋም ብቃቱ የለኝም፤ ሌሎችን ለመርዳትም ራሴን አላዘጋጀሁም::

መጽሐፍ ቅዱስ በድንገት ላጋጠሙ ችግሮች ወዲያውኑ እንደሚያግዝ እንደ መጀመሪያ ደረጃ የሕክምና መርጃ ሳጥን መቈጠር የለበትም:: በእርግጥ ያልተጠበቀ ችግር በሚደርስበት ጊዜ ይረዳል፤ የተለመደው የመጽሐፍ ቅዱስ ሥዕል ግን የምግብ ጉዳይ ነው:: ሰው በጤና አድጎ እንዲጐለምስ የሚገነባና አካላዊ ብርታትን የሚሰጥ ነው፤ (1ቆሮ. 3፥2 ፤ ዕብ. 5፥12-14 ፤ 1ጴጥ. 2፥2)::

ሰዎች ከአሁኑ ጊዜያዊ ሁኔታ በላይ ሊመግባቸው የማይችል ስብከት ቢሰሙ መንፈሳዊ ዕድገታቸው ይቀጭጫል:: ወደ ጠንካራና ክርስቲያናዊ ሕይወት በመሸጋገር ፈንታ ከዕንቅፋት ወደ ዕንቅፋት ይተላለፋሉ:: «ጠቢባን ዕውቀትን ያከማቻሉ» የሚል የጥንት ምሳሌ አለ፤ (ምሳ. 10፥14)፤ ሰባክያን አድማጮቻቸው በሕይወት ጉዟቸው ሊጠቀሙባቸው በሚችሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዕውቀቶች እንዲታነጹ ያደርጋሉ:: ማስታጠቅ፣ ማበረታታትና መገንባት ኀላፊነታቸው ነው፤ (1ቆሮ. 3፥10፤ 14፥5፥20፥26፤ ኤፌ. 4፥11-16)::

# ፩

## የስብከት አዘገጃጀት

### ሰባክያን እንደ ተማሪዎች

መጽሐፍ ቅዱስን ለሌሎች የማስተማር ዕቅድ ካለን ስለምናስተምረው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የጠለቀ ዕውቀት ይኖረን ዘንድ አስቀድመን እንማር፤ በተማሪነታችንም እንትጋ፤ አጠናናችን ለስብከት ዝግጅት ብቻ አይሁን:: የጥናት መረጃችን ቢመችም ባይመችም፥ መጽሐፍ ቅዱስን፥ መጽሐፍ በመጽሐፍ፥ ርእስ በርእስ፥ በደረጃ እናጥናው:: የስብከቱ ጊዜ ሲቃረብ የሚያስቸግረን ማስታዎሻችንን ከማሰባሰቡ ላይ ሳይሆን፥ የምንተውንና የምንይዘውን ከመለየቱ ላይ ነው::

መዘጋጀታችን ተግተን በማጥናት ላይ ብቻ ሳይወሰን ጸሎትንና ራስን መመርመርን ያካትታል:: እንደ ጥንት የእግዚአብሔር ሰባክያን የእግዚአብሔርን ቃል ለሌሎች ከመስጠታችን በፊት የራሳችን ማድረግ ይኖርብናል:: ለእኛ ትርጉም የማይሰጠንን ነገር መደጋገም የለብንም::

እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን ለእስራኤል ሕዝብ እንዲናገር ባዘዘው ጊዜ፥ አስቀድሞ የእግዚአብሔር ቃል ተምሳሌት የሆነውን ጥቅልል መጽሐፍ መብላት ነበረበት:: ከዚያ በኋላ የእግዚአብሔር ቃል መልእክቱ ሆነና በመረዳትና በስሜት አወጀው፤ (ሕዝ. 2፥8 ፤ 3፥3):: ዮሐንስ በአዲስ ኪዳን ዘመን ተመሳሳይ ተሞክሮ ነበረው፤ (ራእ. 10፥8-11):: የዛሬ ሰባክያን ይህን የመሰለ ተሞክሮ ሊኖረን ይገባል:: መልእክቱ መልእክታችን እስከሚሆን ድረስ የእግዚአብሔር ቃል ድርሻችን ይሁን፤ ከዚያም ቃሉን ለማወጅ እንደ ኤርምያስ የጋለ ስሜት ይኖረናል፤ (ኤር. 20፥8-9)::

### የልምምድ ዓላማ

የምንናገረውን የምናምንበት ከሆንን ሰዎች ወዲያውኑ ያውቁታል:: ስለ ሰሙት እውነትም ምስጋና ይሰጣሉ:: የእግዚአብሔር ቃል የሚያስተምረውን ለእነርሱ በግልጽ ማሳወቅ የመጀመሪያው ተግባራችን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በሕይወታቸው ውስጥ እንዴት በተግባር ላይ እንደሚያውሉት ማመልከት ነው:: ይህ በአጠቃላይ የዘወትር ዓላማችን መሆን አለበት:: በዚህ በአጠቃላይ ዓላማችን ውስጥ ለየት ስላሉ ጉዳዮች መናገር እንፈልግ ይሆናል፤ ይህም በጊዜው ፍላጎት ላይና በአድማጮች ይዘት ላይ የተመረኮዘ ነው::

ይህም በተቻለ መጠን በሰፊው እንድናነብ ያሳስበናል:: የምናነበውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ብቻ ሳይሆን ሌላውን ሥነ ጽሑፍም ጭምር ነው::

በማኅበረሰብ ግንኙነቶች፥ በጭውውቶች፥ በጋዜጦች፥ በመጻሕፍት፥ በፊልሞች፥ በመጽሔቶች፥ በሬዲዮ፥ በቴሌቭዥን፥ ወዘተ ውስጥ ብንሳተፍ፥ ሰዎችን ስለሚያሳስቧቸው ነገሮች በበለጠ ግንዛቤ ሊኖረን ይችላል።

ልዩ ልዩ አድማጮች የተለያዩ ፍላጎቶች አሏቸው፤ አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ ወይም ትምህርት የምንመለከትበት መንገድ ከአንዱ አድማጭ ወደ ሌላው ይለዋወጣል:: የስብከት ዝግጅታችንን ከመጀመራችን በፊት የሰዎችን ስብጥርና መጠን ካወቅን ስለምንናገርበት ርእስ፥ ስለምንጠብቀው የመረዳት ደረጃ፥ ምን ዓይነት ተግዳሮት እንደሚያጋጥመን እናውቃለን:: ስብከታችንን ለአድማጩ በሚስማማ ሁኔታ የምናዘጋጅበት ምክንያት፥ እነርሱ ሊሰሙት የሚወዱትን ነገር በማቅረብ ስሜታቸውን ለመሳብ ሳይሆን በሚገባቸውና ከሕይወታቸው ጋር በማዛመድ ሁኔታ ላይ ማዘጋጀታችንን ለማረጋገጥ ነው::

## አጀማመር

ስብከቱ ስለ አንድ ርእሰ ጉዳይ የሚናገር ወይም አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሚያብራራ ሊሆን ይችላል፤ ያም ሆነ ይህ ክፍሉን ደጋግሞ በማንበብ ሐሳቡንም ደኅና አድርጎ በማብላላት ዝግጅቱ ሊከናወን ይገባል:: የዝግጅታችን መጀመሪያ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሆነ ትርጉሙን፥ እንዲሁም እግዚአብሔር የሰጠን መምህራን የጻፏቸውን፥ ብዙ ፍሬም ያፈሩባቸውን መጻሕፍት ትርጓሜና ሌሎችንም ማንበብ ይበጃል::

እነዚህን መጻሕፍት በምናነብበት ጊዜ ጠቃሚ መረጃዎችንና ሐሳቦችን ከሥራቸው እናሰምራለን:: በመጻሕፍት ላይ የሚቆይ መስመር ወይም ምልክት ማድረግ ከማይፈልጉት ሰዎች መካከል ከሆንን ደግሞ በላጲስ ሊጠፋ በሚችል እርሳስ ምልክት ማድረግ እንችላለን::

በተጨማሪም ሁልጊዜ የማይለየን የማስታወሻ ደብተር ሊኖረን ይገባል:: ስለ ዋና ርእሰ ጉዳያችን በምናስብበት፥ በምንጸልይበትና መጽሐፍ ቅዱሳችንን በምናነብበት ጊዜ የምናገኘውን ፍሬ ነገር በማስታወሻችን ልንጽፈው እንችላለን:: ከዚህም በተጨማሪ ይህ የማስታወሻ ደብተር ለዝግጅታችን ድጋፍ የሚሆኑ የመረጃ ምንጮችን (ለምሳሌ የመጣጥፍ ርእሶችን፥ ደራሲውን፥ አሳታሚውን፥ የታተመበትን ቀን፥ የገጾቹን ብዛት) ለመጻፍና ለመያዝ ይጠቅመናል:: በኋላም ጠቃሚ መረጃዎችን ለማግኘት ማውጫ ልናደርጋቸው እንችላለን::

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ማውጫ ያለ መረጃ (ለምሳሌ:- የመጽሐፍ ቅዱስን መጽሐፍ ስም፥ ምዕራፍ፥ ቁጥር) በጽሑፍ በማዘጋጀት ፋይል ማድረግ ተገቢ ነው:: ሌላው ጠቃሚ የማውጫ ዝግጅት ደግሞ በርእስ ጉዳዩ ዝርዝር፥ በፊደል ተራ የሚዘጋጅ ማውጫ (ለምሳሌ :- ደቀ መዝሙር፥ ይቅርታ፥ መንፈስ ቅዱስ፥

ምኩራብ) ተብሎ የሚዘጋጅ ነው:: ቀስ በቀስ በሥርዓትና በጥንቃቄ የተመዘገቡ ማውጫዎች በፍጥነት ያድጋሉ፤ ትልቅ ደረጃ ላይም ይደርሳሉ:: ዕውቀታችን ባደገ ቍጥር እነዚህ ርእሶችም መከለስ አለባቸው:: በእንጻሩ የእኛ አገልግሎት እየሰፋ ሲሄድ እነዚህ ርእስ ጉዳዮች ለዝግጅታችን የላቀ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል::

መጽሐፍ ቅዱስንና ተዛማጅ ምንጮችን ማንበብ ከጀመርንበት ሰዓት ጀምሮ ልንሰብከው ባሰብነው ርእሰ ጉዳይ ላይ ያለን ዕውቀት ይዳብራል:: ይሁን እንጂ መረጃዎችን በማሰባሰብ ብቻ ግንዛቤንና ብቃትን ማግኘት አንችልም:: ስለዚህ ያሰባሰብናቸውን የመረጃ ምንጮች በመገምገም የራሳችንን ሚዛናዊ ማረጋገጫ መስጠት ይኖርብናል::

ወደ ስብከቱ ከመግባታችን በፊት ለዝግጅት በመደብነው ጊዜ ውስጥ፥ ለሳምንታት እንዲያውም ለወራት በዝግጅት ላይ ብንቆይ፥ ስለ ስብከታችን ርእሰ ጉዳዮች፥ ስለ ይዘቱና ስለ መልእክቱ ጥንቃቄን የተሞላ ሥራ ልንሠራ እንችላለን:: በዚህ ዝግጅት ላይ እያለን አንዳንድ ጊዜ ጠቃሚ መስሎ የሚታይ ሐሳብ ወይም ዐረፍተ ነገር ያጋጥመን ይሆናል:: ነገር ግን እንዲህ ያለውን ነገር አበጥረን ሳንመለከት በስብከት ዝግጅታችን ውስጥ ብንጨምራቸው እንቸገራለን:: ምናልባትም በዝግጅታችን ውስጥ የጨመርናቸውን ነገሮች ቆየት ብለን ብናስላስላቸው፥ የተሳሳቱና ሚዛን የማይደፉ በመሆናቸው የማይጠቅሙ ጥንቅሮች ሆነው ይገኙ ይሆናል::

**ለመጻፍ መዘጋጀት**

የስብከታችንን ዝግጅት በተመለከተ እስከዚህ ድረስ ብዙ ካነበብንና ካሰላሰልን በኋላ በተለይም በመርሐ ስብከቱ ውስጥ ሊገቡ ይገባል የምንላቸውን ፍሬ ነገሮች መርጦ ደረጃ የማስያዝ ተግባር ይኖረናል:: ቀድሞ ስናነብና ስናጠና በነበርንበት ጊዜ፥ ልንጠቀምባቸው የምንችል የሐሳብ ጭብጦች አጋጥመውን ይሆናል፤ አሁን እነዚህን ጠቃሚ ጭብጦች የስብከቱ ክፍሎች አድርገን መጻፍ ነው:: ብዙ ጊዜ ከሁለት እስከ ስድስት የሚደርሱ ርእሶች በቂዎች ናቸው:: ርእሶችን የምንሰጣቸው ሐሳቦች ግልጽ ከሆኑ ወደ ፊት በሄድን ቍጥር ሐሳባችንን ቅደም ተከተል ባለው መንገድ ማጎልበት ይኖርብናል:: የስብከት ዝግጀታችንን ለመከፋፈል የሚበጅ ምሥጢራዊ ዘዴ የለም፤ ያካበትነውን ሐሳብ በጥንቃቄ ስንመለከት ግን በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ነጥቦቹ ራሳቸው ብቅ ይላሉ::

የጥናታችንን ፍሬ ነገሮች በስብከቱ ውስጥ በምናቀርብበት ጊዜ፣ ከጥናቱ ያካበትናቸውን ሐሳቦች፥ ይጠቅማሉ የምንላቸውን ነጥቦች በስብከታችን ይዘት ውስጥ በራሳችን አባባል መጻፍ አለብን:: ይህን በምናደርግበት ጊዜ በጥናታችን ወቅት የሐሳብ ምንጭ በሆኑን መጻሕፍት ውስጥ ያሰመርንባቸውን ፍሬ ነገሮች

አሁን ልንጠቀምባቸው እንችላለን። ምናልባትም ያስመርንባቸውን ሐሳቦች ሁሉ ልንጠቀምባቸው አንችል ይሆናል። ይህንንም የምናደርግበት ምክንያት ምናልባት ሐሳቦቹ ከምናዘጋጀው ስብከት ጋር ተያያዥነትና ፍሰት ስለሌላቸው ሊሆን ይችላል። ይህ ብቻም አይደለም በዝግጅታችን ውስጥ ያሠመርንባቸው ሐሳቦች ሁሉ ጠቃሚነታቸው አጠራጥሮን ይሆናል። ይጠቅሙናል የምንላቸውን ሐሳቦች መርጠን ከጻፍንና አይጠቅሙንም ያልናቸውን ሐሳቦች ከተውን በኋላ የመስመር ምልክቶቹን በላጲስ አጥፍተን መጻሕፍቱን በነበሩበት መደርደሪያ ላይ መልሰን ማስቀመጥ አለብን። ከዚህ በኋላ ያካበትናቸውን ሐሳቦች ጠርዝ አስይዘን፥ አቀማመጣቸውን በሥርዓት በማድረግ፥ የምናስቀራቸውን በማስወገድ፥ የሚጨመረውን በማከል ማብራሪያ የሚያስፈልገውን በራሳችን ስልት በማብራራት ነጻ ሆነን መሥራት እንችላለን፤ ይህን ስናደርግ ፍሬ ሐሳቦቹን ያገኘንባቸውን የዋቢ መጻሕፍት ስም መጻፍ አይኖርብንም።

ምንም እንኳ የሌሎች ሰዎችን መጻሕፍት በምንጭነት የምንጠቀም ብንሆንም ደጋግመን በእነርሱ መጠቀም የለብንም። ትኩረት ልንሰጠው የሚገባ ለመጽሐፍ ቅዱስ እንጂ ሰዎች ስለ ጻፉት ድርሰት አይደለም። በስብከቱ ዝግጅት ከመጽሐፍ ቅዱስ በተገኘው ግንዛቤና ተግባራዊ ተሞክሮ፥ ዓላማው፥ አንድነቱ በአድማጩ ዘንድ ጣዕም ያለው ሆኖ ሲገኝ ይገባዋል። እንደዚሁም ስብከቶቻችን በአድማጮች ዘንድ ክብደት እንዲኖራቸው ከተፈለገ ከራሳችን እምነት መነሣት ይኖርባቸዋል እንጂ ከሌላው ሰው ሐሳብ በቀጥታ መቀዳት የለባቸውም። በዝግጅታቸውና በሐሳባቸው ከሌሎች ሰዎች የተወሰዱ ስብከቶች ተአማኒነትም ተቀባይነትም የላቸውም።

ስብከታችንን በጣም ብዙ በሆኑ ሐሳቦች ከመወጠር ልንጠነቀቅ ይገባል። ይህን የምንልበት ምክንያት የምናነባቸውና የምናጠናቸው ሐሳቦች በጣም ይስቡንና በማስታወሻ ያሰፈርናቸውን ነጥቦች በሙሉ በስብከቶቻችን ውስጥ በማካተት ምእመናን እንዲሰሙት ማድረግ እንፈልጋለን። እነርሱ ግን ያቀረብንላቸውን ሁሉ የመቀበል ፍላጎት ላይኖራቸው ይችላል። ስለዚህ ባለን የስብከት ጊዜ ውስጥ በጣም ሊጠቅሟቸው ይችላሉ በምንላቸው ፍሬ ነገሮች ላይ መወሰን ይኖርብናል።

በርከት ያሉ ርእሰ ጉዳዮችን የያዙ ፍሬ ነገሮችን ጽፈን ብናስቀምጥ ከእነዚህ ነጥቦች የምናገኘው ዕውቀት ዘና ብለን፥ ሳንጨነቅ እንድንሰብክ ያግዘናል። ሆኖም ቀደም ሲል እንደጠቈምነው በጥናታችን ጊዜ በማስታወሻ ላይ የጻፍናቸውን ወይም በልባችን ውስጥ የያዝናቸውን ሐሳቦች በሙሉ በስብከቶቻችን ውስጥ መጠቀም አንችልም። በስብከታችን ውስጥ የተጠቀምነው ሐሳብ የጥናታችን አንድ አራተኛ ቢሆን ስለ ቀሪው ሐሳብም በቂ ዕውቀት ስላለን ስብከቱን ዘና ብለን፥ በራስ በመተማመን፥ በበቂ ሁኔታ ማቅረብ እንችላለን።

## የጽሑፍ ጥቅም

በአማርኛ የሚዘጋጅ ጽሑፍ ከአማርኛ ንግግር ጋር አንድ ሊሆን አይችልም። ጽሑፋዊ ዝግጅት የሚደረገው በቃላት የተቀነባበረና በቃል ለማስታወስም የሚያስችል ስብከት ለማዘጋጀት ተብሎ ሳይሆን ሐሳባችንን ግልጽ ለማድረግ ነው። አንድን ሐሳብ በጽሑፍ ማስፈር ባንችል፥ ሊገባ በሚችል ቋንቋም ባንጽፍ፥ ምናልባት እኛም በሚገባ አልተገነዘብነውም ይሆናል። ለማስተላለፍ የምንፈልገውን ማንኛውንም ሐሳብ በግልጽና በቀላል ቋንቋ ማስተላለፍ አለብን።

ባጠቃላይ ቀላል ቃል እያለልን በከባድ ቃል መጠቀም የለብንም። ለምሳሌ፦ «ጣረ» በማለት ፈንታ «ሞከረ»፥ «ተከሰተ» በማለት ፈንታ «ሆነ» ማለት እንችላለን። የሰባኪው ቃላት ትክክለኞችና የተለያዩ መሆን አለባቸው። ስለ ቃላት ትርጉምና አጠቃቀም ጥሩ መዝገበ ቃላትና ሌሎች መጻሕፍት ሊኖሩን ይገባል።

ዐረፍተ ነገሮቻችን ውስብስብ በመሆን ፈንታ ቀላልና ግልጽ፥ የአጻጻፍ ስልታችን ረቂቅና ምስጢራዊ ከመሆን ይልቅ ግልጽና ቀጥተኛ፥ የሐሳብ አገላለጻችንም የቀለም ትምህርት በመሆን ፈንታ በተግባር ላይ ያተኮረ ሊሆን ይገባዋል። «እውነት አስፈላጊ ባሕርይ ነው» በማለት ፈንታ «ሁልጊዜ እውነትን መናገር አለብን» ማለቱ የተሻለ ይሆናል። እንደዚሁም ምእመናን ብዙ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚሰሟቸውን፥ ግን ትርጉማቸውን የማይገነዘቧቸውን ቃላት ለመተርጐም መጣር፥ ማብራራት ወይም በመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት መተካት ይቻላል። እንደ «ኀጢአት» እና «ድነት» የመሳሰሉት መወገድ አይችሉም፤ እነዚህን ቃላት ስንጠቀም ሰዎች ገብቷቸው እንደ ሆነ ማረጋገጥ አለብን።

ይህ በቃላት ላይ የሚደረግ የማብራራት ተግባር በይበልጥ «ጽድቅ» እና «መቤዠት» የሚለውን ይመለከታል። አንድ ጊዜ ካብራራናቸው በኋላ ግን በተተኪ ቃላት ወይም ሐረጋት መጠቀም እንችላለን። አሮጌውን ቃል በትክክል የሚፈታ አቻ የሆነ ዘመናዊ ቃል ወይም ሐረግ ካለ በመተካት ለምሳሌ «ሥጋ» በማለት ፈንታ «ኀጢአተኛው የሰው ልጅ ተፈጥሮ» ብለን መጠቀም እንችላለን።

የጽሑፍ ሥራ በንግግር ላይ የምንጠቀምባቸውን አላስፈላጊ የሆኑ ቃላትን ተረድተን እንድናስወግዳቸው፥ ስለ ራሳችን አስጊ ሁኔታዎች እንድናስብ፥ የልምድ ሰባኪነትን ቋንቋም እንድናስወግድ ይረዳናል። አንዳንድ ቃላትና የአገላለጽ ስልቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚሰሙ ዘይቤዎች ሆነዋል፤ ነገር ግን እነዚህ አባባሎች በዕለታዊ ንግግሮቻችን ውስጥ አይደመጡም። በተለይም በስብከት ዝግጅታችን ውስጥ በጽሑፍ የምናሠፍራቸው ቃላትም ሆኑ ሐረጋት ትርጉማቸው ከባድና ዙሪያ ጥምጥም ሆኖ አድማጩን እንዳያስቸግር ግልጽና ቀላል በሆኑ ቃላትና ሐረጋት መተርጐም አለብን። በጥቅሉ በሕዝብ ዘንድ የተለመዱ ቃላትንና አባባሎችን በተቻለ መጠን ልንጠቀምባቸው ይገባናል።

## ትምህርቱን ከሕይወት እንቅስቃሴዎች ጋር ማዛመድ

ሁለቱ ጥንድ የስብከት ዓላማዎች የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት ለአድማጮቹ ማሳወቅና ያወቁት ነገር ለእነርሱ ምን ያህል ጥቅም እንዳለው ማስረዳት ሊሆኑ ይገባል:: የትምህርቱ ዋና ጥቅም በተግባር ላይ የማዋሉ ሁኔታ ነው፤ ስለሆነም ሰባኪው ትምህርቱን ከአድማጩ ዕለታዊ የኑሮ ሁኔታ ጋር በማዛመድ ያቀርባል:: በዚህም ከአድማጩ ጋር ተዛማጅ የሆነውን የሕይወት ጥያቄ የሚመልስ ቁም ነገር ያመለክታቸዋል::

ስብከታችንን ከጅማሬ እስከፍጻሜ ከሕይወት እንቅስቃሴዎች ጋር ተያያዥነትና ተዛማጅነት እንዲኖረው የምናደርግበትን አጋጣሚ መፈለግ ይገባናል:: እንዲህ ሲባልም ስብከታችን ተዛምዶን አነፍናፊ መሆን አለበት ማለት አይደለም፤ ወይንም ከሕይወት ጋር የማዛመዱን ሁኔታ ከእያንዳንዱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ወይም ትምህርተ መለኮት አገላለጽ ጋር ማያያዝ አለብን ማለትም አይደለም:: መጽሐፍ ቅዱስን አብራርተን ብናቀርብ ያኔ ሰዎች በስብከቱ ውስጥ ሊዛመዱ የሚገባቸውን ነጥቦች ሊገነዘቡ ይችላሉ:: ይህን ሲሰሙና ሲገባቸውም ከዚህ በፊት ይህን ለምን እንዳላስተዋሉት ይደነቃሉ::

አጭር÷ ግን ፍሬያማ ትምህርት ስንሰጥ÷ ወይም በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረተ ጥያቄ ስናቀርብ÷ ትምህርቱን ከሕይወት ጋር የማዛመዱ ተግባር ውጤታማ ይሆናል:: አድማጮቻችንን በሚሰሙት ስብከት ላይ የራሳቸውን ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ግንዛቤ ያላቸው አድርገን መቁጠር አለብን:: አንድ ጊዜ ግልጽ አድርገን የተናገርነውን ተመልሰን በተጋነነ ሁኔታ ክብደት ሰጥተን ብንናገር የአድማጮቹ ስሜት ካሰብነው በተቃራኒው ይሆናል:: አድማጮቻችንን በንቀት እንዳንናገራቸው ወይም የስድብ ሁኔታ እንዳናሰማቸው መጠንቀቅ አለብን::

በሚቻለን ጊዜና ስፍራ ሁሉ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል ምክርና ተግሣጽ ከዕለታዊ ኑሮ ጋር ሊዛመዱ የሚችሉትን ምሳሌዎች እንናገራለን:: ጌታ ኢየሱስ እርሱን ማገልገል ማለት የተራበን ማብላት÷ ድኾችን ማልበስ÷ ባይታወሮችን ማጽናናትና የተለየ ችግር ያለባቸውን መርዳት እንደ ሆነ በገለጸ ጊዜ ስለዚህ አስገንዝቧል፤ (ማቴ. 25÷34-35):: ይህንን ሐሳብ÷ አንድ አይሁዳዊ የሕግ አዋቂ «ባልንጀራ» የሚለውን ቃል እንዲያብራራለት በጠየቀው ጊዜ በመለሰው መልስ እንደ ገና ደግሞታል፤ (ሉቃ. 10÷27-37):: ኢየሱስ ለዚህ የሕግ አዋቂ የደጉን ሳምራዊ ታሪክ ከነገረው በኋላ «አንተም ሂድና እንዲሁ አድርግ» አለው::

የመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ሰባኪዎች በትምህርታቸው ያስተላለፏቸውን መመሪያዎች እንዴት በተግባር ላይ እንደሚያውሉ ያብራሩላቸው ነበር:: ሐዋርያው ያዕቆብ ክርስቲያኖች ከሰዎች ጋር ባላቸው ግንኙነት ላይ አድልኦ እንዳያደርጉ ሲያስጠነቅቃቸው ሳለ÷ የጠቀሰው ምሳሌ የተሳሳተ ጠባያቸውን

የሚያመለክት ነበር:: ምክንያቱም በማኅበረሰቡ ውስጥ በዝቅተኛ ደረጃ የሚታዩትን በመናቅ ሀብታሞችን ያከብሩ ስለ ነበረ ነው፤ (ያዕ. 2፥1-7):: ዮሐንስ ወንድሞቻቸው የሆኑ ክርስቲያኖችን እንዲወዱ በጻፈ ጊዜ ይህ ትምህርት የተራቈቱትን ማልበስ፥ ገንዘብ ለሌላቸው ገንዘብ መስጠት መሆኑን በግልጽ ነግሯቸዋል፤ (1ዮሐ. 3፥16-17)::

የዛሬዎቹ ሰባኪያን የመጀመሪያውን ምዕተ ዓመት ሰባኪያንን አርአያ ልንከተል ይገባናል:: የስብከታችንን ዝግጅትና አቀራረብ ስናስብ መልእክታችን ጊዜውን የተከተለና ተግባራዊ ሊሆን የሚችል መሆን አለበት:: ይህን ለማድረግ የምንወስደው ጥንቃቄ ሰዎችን ለመሳብ ወይም በእነርሱ ዘንድ ተወዳጅነትን ለማግኘት ብለን የምናደርገውን ሙከራ ለማስቀረት፥ በጣም የተለመደና ከዕለታዊ ተሞክሮ ጋር ግንኙነት የሌለውን አተገባበር እንዳንጠቀም ይረዳናል::

## የማብራሪያዎች ጥቅም

ማብራሪያዎች ለአድማጮቹ የአዕምሮ ዕረፍትን ከመስጠታቸው በተጓዳኝ ስብከትን ከዓለማዊው ማዕበል ይጠብቃሉ:: ሆኖም የምናቀርባቸው ማብራሪያዎች ከመጽሐፍ ቅዱሱ ክፍል ወይም ከምናስተምረው ትምህርት ጋር የሚስማሙ መሆን አለባቸው፤ እንደዚሁም በአንድ ጊዜ አንድን ፍሬ ነገር ብቻ ለማብራራት የሚጠቀሙ ሊሆኑ ይገባል:: በአንድ ማብራሪያ ብዙ ፍሬ ነገሮችን ለመፍታት፥ ለማብራራት ብንሞክር በራሳችን ላይ ችግር እናስከትላለን:: ከዚህ በላይ የቀረቡ የአዲስ ኪዳን ምሳሌዎች እንደሚያመለክቱት በአንዳንድ ሁኔታ የማብራሪያ ምሳሌዎች በመስጠት ከውጤቱ መመሪያዎችን ማግኘት እንችላለን፤ በሌላው ሁኔታ ደግሞ መመሪያዎችን በመግለጽ ምሳሌዎችን ማቅረብ እንችላለን::

አንድ ታሪክ አስደሳች ስለ ሆነ ብቻ ለመናገር እንዳንገፋፋ መጠንቀቅ ይገባናል:: ይህን ብናደርግ፥ የሰዎችን የማድመጥ ፍላጎት ሊስብ ይችል ይሆናል፤ ነገር ግን ስብከቱን በሙሉ ያበላሸዋል:: አድማጩ ታሪኩ እንዲያብራራ በምሳሌነት የቀረበለትን ፍሬ ነገር ሳይገነዘብ የተተረከውን ታሪክ ብቻ ቢያስታውስ ታሪኩን ለማብራራት በጥቅም ላይ የዋለበትን ዓላማ ብቻ ሳይሆን የሚያብራሪያው ቁም ነገርም መና ቀረ ማለት ይቻላል:: ልዩ የሆኑ ታሪኮችን ለማብራሪያነት ስንጠቀም ልዩ ጥንቃቄ ያስፈልጋል:: ስሜትን ብቻ የሚሰቅል ታሪክ እምብዛም ከሕይወት ጋር ሊያያዝና ሊዛመድ አይችልም:: አድማጮችም ቢሆኑ ይህን የመሰለው ታሪክ ከሕይወት ጋር ያለውን ተያያዥነት ትኩረት አይሰጡትም::

## አንዳንድ የብሉይ ኪዳን ምሳሌዎች

አብዛኛውን የስብከት ጊዜያችንን የመጽሐፍ ቅዱስን ክፍል ለማብራራት ብንጠቀም ማብራሪያዎቻችንን ካሰብነው ባነሰ መጠቀም ያስፈልጋል:: ይህ ሊሆን

የሚችልበት ምክንያት መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ በምሳሌያዊ ማብራሪያዎች የተሞላ በመሆኑ ነው:: ምሳሌዎቹም ከተጨባጭ የሕይወት ሁኔታዎች ጋር ይዛመዳሉ፤ ቋንቋውም ሥዕላዊ ቋንቋ ነው::

ለብዙ ሰዎች እምብዛም ስሜታቸውን የማይስበው የሙሴ ሕግ ነው፤ ያም ሆኖ አብዛኛዎቹን ሁኔታዎች በሥዕላዊ ማብራሪያ ማቅረብ ይቻላል፤ ለምሳሌ በቤት ውስጥ የሚያገለግል ባሪያ (ዘፀ. 21÷1-6)÷ አንዱ ሰው ሌላውን ሲመታ (ዘፀ. 21÷12-14)÷ ሁለት ሰዎች ሲጨቃጨቁ (ዘፀ. 21÷18-19)÷ በጉድጓድ የወደቀ በሬ (ዘፀ 21÷33)÷ ቤት ሲሰረስር የተገኘው ሌባ (ዘፀ. 22÷2)÷ ገበሬ ማሳውን ሲያቃጥል (ዘፀ. 22÷6)÷ ሌሎችንም መመልከት ይቻላል:: በተመሳሳይ ሁኔታ የታሪክ መጻሕፍት እውነተኛውን የሕይወት ገጽታ ያመለክታሉ፤ ትረካዎቻቸውም ባብዛኛው መስህብ ያላቸው ናቸው:: የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ራሱ እውነተኛና ተጨባጭ ስለ ሆነ ድጋፍ የሚሰጥ ተጨማሪ ጥናታዊ ማብራሪያ ለመፈለግ ወደ ሌላ ስፍራ ብንሄድ አስፈላጊነቱ እምብዛም ነው::

ጥልቅ የሆነ የመንፈሳዊ ስሜት መገለጫ የሆኑት የዳዊት መዝሙራትም እንኳ ሐሳባቸውን ለማስተላለፍ የሚጠቀሙባቸው ምሳሌያዊ ማብራሪያዎች ምድራዊ ናቸው፤ ከእነዚህም አብዛኛዎቹን በተምሳሌትነት በቀላሉ መመልከት ይቻላል:: ለምሳሌ ሰዎች በቡድን ሆነው ሲነጋገሩ (መዝ. 1÷1)÷ በወንዝ ዳር የተተከሉ ዛፎች (መዝ 1÷3)÷ በነፋስ ተጠራርጎ የተወሰደ ገለባ (መዝ. 1÷4)÷ ዐመፀኞች አንድን ንጉሥ ከዙፋን ለማውረድ ማደማቸው (መዝ 2÷2)÷ የሰንሰለቶቹ መበጠስ (መዝ. 2÷3)÷ የሸክላ ዕቃ መሰበር (መዝ. 2÷9) እነዚህን የመሳሰሉ ተምሳሌቶች ቊጥር በቊጥር÷ ምንባብ በምንባብ÷ በየመዝሙራቱ ውስጥ ተጽፈው ይገኛሉ::

በጥበብ መጻሕፍት ውስጥ የተጻፉ ሥዕላዊ ማብራሪያዎችና ልዩ ልዩ የማስገንዘቢያ ተምሳሌቶች የበለጠ ማራኪዎችና ስሜትን የሚስቡ ናቸው:: ለምሳሌ ለአንድ ወጣት ወጥመድ ያዘጋጀችዋን አመንዝራ ሴት (ምሳ. 7÷6-23)÷ ግብዣ ያዘጋጀችዋን ባለጸጋ ሴት (ምሳ. 9÷1-6)÷ በባልንጀሮቹ ዘንድ ጠብን የሚያባብሰውን አዋኪ ሰው (ምሳ. 26÷17-25)÷ የወፎችን ወጥመድ (ምሳ. 1÷17)÷ ስለ ወቅቶቹ ማውጋትን (ምሳ. 25÷13-14) በየጎዳናው÷ በየገበያው ጮኾ መጣራትን (ምሳ. 1÷20-22)÷ ... ወዘተ የመሳሰሉትን ማግኘት እንችላለን::

የብሉይ ኪዳን ነቢያት ሰባክያን ነበሩ፤ ስብከቶቻቸውም በጥንቃቄ የተዘጋጁና የአድማጮችን ጆሮ የሚስቡ ነበሩ:: አንድ ምዕራፍ የተለያዩ የማብራሪያ ሥዕላዊ ተምሳሌቶችን ይዟል፤ ለምሳሌ :- ስለ እርሻ ሙያ እንስሳት (ኢሳ. 1÷3)÷ የታመመ ሰው (ኢሳ. 1÷5-6)÷ የገጠር አካባቢ (ኢሳ. 1÷7)÷ በወይን ተክል ውስጥ ያለ ዳስ (ኢሳ. 1÷8)÷ የተከበበች ከተማ (ኢሳ. 1÷8)÷ በዓልን

በሃይማኖታዊ ሥነ ሥርዓት ስለ ማክበር (ኢሳ 1:11-15)፥ ስለ መታጠቢያ ስፍራ (ኢሳ. 1፥16-18)፥ አመንዝራዎች፥ መበለቶች፥ ልዑላንና ሌቦች (ኢሳ. 1:21-23)፥ ብርን ከዝገት ማስለቀቅ፥ ማጥራት (ኢሳ. 1:22ና25)፥ የሞቱ ዛፎች (ኢሳ. 1:30)፥ የሚቃጠል ቆሻሻ (ኢሳ. 1:31) ያሉትን መመልከት ይቻላል።

እነዚህ የብሉይ ኪዳን ማብራሪያዊ ተምሳሌቶች መልእክታችንን በዙሪያችን ካለው ዓለም ጋር ከማዛመድ ያለፈ ቁም ነገርን ያሳስቡናል። መጽሐፍ ቅዱስን ባለበት ሁኔታ አካቶ ከያዛቸው ፍሬ ነገሮች ተነሥተን ብንናገር ትምህርቶቻችንና ስብከቶቻችን መጽሐፍ ቅዱሳችን በየክፍሉ በያዛቸው ትምህርታዊ ተምሳሌቶች የበለጸጉ ይሆናሉ። በየከፍሉ በቂ የሆኑ የማብራሪያ ተምሳሌቶች በመጽሐፉ የተካተቱ ስለ ሆነ፥ እነዚህን ተምሳሌቶች ፍለጋ የትም መባዘን አይኖርብንም፤ ተምሳሌቶቹም ሆኑ ምሳሌዎቹ እዚያው ውስጥ አሉ።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች በጽሑፍ ያስተላለፉልንን ተምሳሌታዊ ወይም ምሳሌያዊ መረጃዎችን በዐይነ ልቡናችን ተመልክተን በተግባር ላይ የማዋል ልምድ ይጠበቅብናል። የእነዚህን ተምሳሌቶች ወይም የማስተማሪያ ምሳሌዎችን ጥቅም በምንገልጽበት ጊዜ አድማጮቻችን የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል ሕይወት ዘርቶ በፊታቸው ሲቆም ያገኙታል። ለምናቀርባቸው ስብከቶች ወይም ትምህርቶች ማብራሪያነት እንዲያግዙ በሥዕላዊ ተምሳሌቶች ተጠቅመን አድማጮቻችንን ለመሳብ ብዙ ጥረት አያሻንም ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱሳችን እነዚህን ነገሮች ሁሉ ያካተተ ስለ ሆነ ነው። ታሪኮችን በመተረክ አድማጮቻችን ከምናዝናናቸው ወይም የወቀሳ ቃል በመናገር ከምናስለቻቸው ይልቅ መጽሐፍ ቅዱሳችንን ከነማብራሪያው አቅርበን ስለ ራሱ እንዲናገር እንተወው።

## ኢየሱስና የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች

የአዲስ ኪዳን መጻሕፍትን ስንመለከት ጌታ ኢየሱስ አዘውትሮ ሥዕላዊ በሆኑ ቃላት ሲጠቀም እናገኘዋለን። አድማጮቻችን ጌታ ኢየሱስ ሲያስተምር ይጠቀምባቸው ስለ ነበሩት ዘዴዎችና ስለ ትምህርቱ ማወቅ እንደሚገባቸው መዘንጋት አይገባም። የኢየሱስን ትምህርቶች ረቂቅ አድርጎ በማቅረብ ፈንታ በተምሳሌት ማስገንዘቢያ ተጠቅመን ጭብጥ ባለውና ከሕይወት ጋር ተያያዥ በሆነ ዘዴ እናስተምር። ኢየሱስ የተጠቀመባቸውን ዛሬ በምናዘጋጃቸው መርሐ ስብከቶች ውስጥም ሊጠቅሙ በሚችሉበት ሁኔታ ልንጠቀምባቸው ይገባል።

ጌታ ኢየሱስ እንጀራ ስለምትጋግረው ሴት (ማቴ. 13፥33)፥ እርሻውን ስለሚንከባከበውና ስለሚያስተዳድረው ባለቤት (ማቴ 21፥33-41) የተናገረውን ወስደን አድማጮቻችን የትዕይንቱ ሥዕላዊ አገላለጽ እንዲኖራቸው ማድረግ እንችላለን። ለአድማጮቻችን የሚሆን መንፈሳዊ ትምህርትን እንሻ ይሆናል፤ ይሁን እንጂ ይህን ስናደርግ የኢየሱስን ተግባራት ከዓለማችን ተጨባጭ ሁኔታ ውጪ

ማድረግ የለብንም:: ስለዚህ መንፈሳዊ ትምህርቶቻችን በግብር ይውጣ ስሜት የተዘጋጁ ሳይሆኑ÷ ጌታ ኢየሱስ ከነበረበት ጊዜና ተመክሮ የመነጩ መሆን አለባቸው:: ባጠቃላይ ጌታ ኢየሱስ ያኔ ሲመላለስ የነበረው ዛሬ በአካባቢአችን ከሚያጋጥሙን ሰዎች ጋር በሚመሳሰሉ ኅብረተሰቦች መካከል ነበር::

የትምህርተ ክርስትና ቃላት እንኳ ባብዛኛው የተገኙት ከገሃዱ ዓለም እንቅስቃሴዎች ነው:: ጳውሎስ በጸጋ ስለ መጽደቅ ያስተማረው ትምህርት÷ ድባቡ የተገኘው ከፍርድ ዐደባባይ ነበር፤ ይህ የፍርድ ዐደባባይ ወይም ችሎት ዳኛው ንጹሑን በነጻ የሚለቅበት በአንጻሩ በበደለኛው ላይ የሚፈርድበት ሸንጎ ነው፤ (ሮሜ 3÷26፤ 8÷33):: የማደጎ ልጅን እንደ ራስ ልጅ ስለ መቀበል ያቀረበው የወቅቱ ልምድ መነሻ ሐሳቡ÷ መካን የሆኑ ወይም ልጅ የሌላቸው ባለትዳሮች የሌላ ሰውን ልጅ በማደጎ ተቀብለው÷ ይህ ልጅ አድጎ ታማኝነቱን ሲያረጋግጥ የእነርሱ ፍጹም ወራሽ ከሚሆንበት÷ የቄየ ሥርዓት የተገኘ ነው፤ (ገላ. 3÷26 ፤ 4÷4-6):: መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ክርስቲያን እውነት በሚናገርበት ጊዜ ከተለመዱት ትዕይንታዊ ቃላት ረቀቅ ወዳለው የሥነ መለኮት ትምህርት ያሸጋግረናል::

እኛም ትምህርተ መለኮትን ስናስተምር የመጽሐፍ ቅዱስን ተምሳሌታዊ ማብራሪያ በመጠቀም ትምህርታችንን ያለ እንዳች ዕንቅፋት ውጤታማ በሆነ መንገድ ወደ አድማጮቻችን ማስተላለፍ እንችላለን:: ከዚህ የበለጠ ተምሳሌታዊ የማብራሪያ ዘዴ ቢያስፈልገን ከዛሬው ጊዜ ጋር ተመጣጣኝ የሆኑ ምሳሌያዊ ማብራሪያዎችን ማቅረብ እንችላለን:: ታዲያ ይህን በምናደርግበት ጊዜ ለትምህርታችን ጠቃሚና ውጤታማ የሚሆኑ ተምሳሌታዊ ማብራሪያዎች ከታሪኮች ይልቅ ማነጻጸሪያዎች ሊሆኑ እንደሚገባ ማስታወስ ይገባል:: ይኸውም ስለ ተጨባጩ ክስተት ከመተረክ ይልቅ አንዱን ነገር ከሌላው ጋር ማነጻጸሩ ይመረጣል ማለት ነው:: አብዛኛዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ሥዕላዊ ማብራሪያዎች ተመሳሳይነት አላቸው:: ለምሳሌ :- ድነትን ወይም መቤዠትን በተመለከተ የአዲስ ኪዳን ንጽጽር የመጣው ከባርነት ተግባርና ተሞክሮ ነው:: አንዱ ሰው አንድን ባሪያ ከምርኮ ለመቤዠት÷ ለማስለቀቅ ዋጋ እንደሚከፍል ሁሉ ጌታ ኢየሱስም እንደዚሁ አማኞችን ከኀጢአት ባርነት ነጻ ለማውጣትና ለመቤዠት በሞቱ ዋጋ ከፍሏል፤ (ገላ. 3÷13 ፤ 5÷1 ፤ 1ጴጥ. 1÷18-19)::

የዛሬ ዘመን ሰዎች ከቀድሞ ሰዎች ይልቅ እውነትን በምናባቸው ለመሳል ክህሎቱ ይጐድላቸዋል፤ (ምናልባትም ይህ የሆነበት ምክንያት ዛሬ ሆን ተብሎ የተዘጋጀ የማዝናናት ሁኔታ ስላለ ሊሆን ይችላል):: ስለዚህ ስብከታችንን በምናቀርብበት ወቅት ለግንዛቤያችን እንዲረዳ ሥዕላዊ ማብራሪያውን አድምቀን ማቅረብ ይኖርብናል:: ከሁሉ አስቀድሞ ግን በምናነብበትና በምናጠናበት ጊዜ የራሳችንን አዕምሮአዊ ሥዕል አድምቀን የመገኘትን ባሕርይ ማዳበር ይገባናል:: ስለምናነበው ነገር ምናባዊ ሥዕል ከሌለን አድማጮቻችን ይኖራቸዋል የሚለው ተስፋ የመነመነ ይሆናል::

**የምስባክ ማስታወሻዎች**

ሁላችንም የስብከት ማስታወሻዎቻችንን በተለያዩ መንገዶች ጽፈን እንይዛለን፤ እነዚህን በስብከቱ ዕለት ወደ መስበኪያው ቦታ ይዘን የምንወጣውን ማስታወሻ ወይም የስብከቱ ሐሳብ መከታተያዎችን በእጅም ይሁን በታይፕ ወይም በኮምፒውተር በማንኛውም ዓይነት እናዘጋጃቸው:: ግን በግልጽ የተጻፉና በዐይናችን እየቃኘን በቀላሉ ልናያቸው የምንችላቸው፥ የጽሑፍ ዐይነቶች መሆን ይገባቸዋል:: ስለሆነም ከምናዘጋጃቸው ማስታወሻዎች በተለይም ከፍሬ ሐሳቦቻቸው ግርጌ በተለያዩ ቀለማት ብናስምርባቸው መስመሮቹም ችፍግ እንዳይሉ ብናራርቃቸው ዐይን ግቡ ሊሆኑና በቀላሉ ሊታዩን ይችላሉ::

ቀደም ሲል እንደገለጽነው ሁሉ በራስ በመተማመን የተሳካ ስብከት ማቅረብ የምንችለው ስለምንናገረው ርእሰ ጉዳይ በሚገባ ስናውቅ ብቻ ነው:: ይህን ጥረት የሚሻውን ተግባር የሚተካ ሌላ ነገር የለም:: ስብከት በምናቀርብበት ርእሰ ጉዳይ ላይ የሚፈለገውን ያህል፥ አስቀድመን ብናነብና ብናጠና፥ ለስብከታችን የሚጠቅሙንን ነጥቦችም በጽሑፍ ብንይዝ፥ ምናልባት ከዚህ ከምንይዘው ማስታወሻ ለመርሐ ስብከታችን ይሆነን ዘንድ አዘጋጅተን ወደ መድረክ የምንወጣው አንድ ወይም ሁለት ገጽ ብቻ ነው:: ማስታወሻዎቹ የሚረዱን ስብከቱን በቀጠልን መጠን የያዝናቸውን ነጥቦች ያለምንም ጉድለት በቅደም ተከተል እያሰብን እንድንጠቀምባቸው ነው:: በተጨማሪም ቁልፍ የሆኑ ቃላትን፥ ጥቅሶችንና ሐሳቦችን ጽፈን መያዛችንም ሆነ በቃል ማጥናታችን፥ አንድ ነገር መግለጽ በፈለግንበት ሰዓት ሁሉ ጠቃሚ ሆኖ እናገኘዋለን::

በጽሑፍ የምንይዛቸው ወይም በቃል የምናጠናቸው ልዩ ልዩ ሐሳቦች ለስብከታችን መክፈቻ ወይም መዝጊያ ለሚሆኑ ዐረፍተ ነገሮች ይጠቅሙናል:: ንግግራችንን ስንጀምር የመርበትበት ሁኔታ እንዳይገጥመን እነዚህን ቃላት የስብከታችንን መግቢያ ማድረግ እንችላለን:: ሆኖም እነዚህ ዐረፍተ ነገሮች እጅግ የተለዩ ናቸው ማለት አይደለም፤ ዋናው ቁም ነገር ወደ መድረኩ ከወጣን በኋላ የምንናገራቸውን የመጀመሪያና የመደምደሚያ ቃላት በሚገባ ማወቃችን ነው::

አንዳንድ ጊዜ የስብከቱ መግቢያ ሐሳብ አድማጮችን ሊስብ በሚችል ምሳሌ ወይም ጥበባዊ ንግግር ላይ ሊመሠረት ይችላል:: ይህ አመሠራረት አድማጮቹን ለሚቀጥለው ስብከት ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ መምራት አለበት:: ታዲያ እነዚህ ለመግቢያው በር ከፋች ሆነው የሚቀርቡ ቃላት የታሰበውን አካሄድ ሳያዛቡ ወደ ስብከቱ ሰተት አድርገው የሚያደርሱ መሆን አለባቸው፤ ይህን ባያደርጉ አድማጮችን በሚቀጥለው ስብከት ላይ ያስናክሏቸዋል:: የስብከቱ መድምደሚያ ቃላት አድማጮችን ለተግባር ለማዘጋጀት ጥሪ በሚያቀርቡ ሐሳቦች፥ በመጠይቆች፥ ወይም ከመጽሐፍ ቅዱስ በተወሰዱ ጥቅሶች ላይ ሊመሠረቱ ይችላሉ:: ሆኖም የመደምደሚያ ቃላት የቀረበውን ስብከት ሳያፈርሱ

ከስብከቱ ጋር የሚስማሙ መሆን አለባቸው። የስብከቱን ሙሉ ሐሳብ አጠቃለው የሚያቀርቡና ልብን የሚነኩ የመጨረሻ ቃላት ሊሆኑም ይገባል።

ወደ ስብከቱ መግቢያ የሚሆን የመንደርደሪያ ሐሳብ ማዘጋጀቱ ለሰባኪውም ሆነ ለአድማጮች መልካም ነው፤ ነገር ግን ይህ የመንደርደሪያ ሐሳብ አጭር፥ ከስብከቱ አጠቃላይ ይዘት ጋር የተያያዘ መሆን አለበት። ሐሳቡ ረቂቅ ከሚሆን ይልቅ ግልጽነት ያለበት መሆን ይኖርበታል። ከባድ ቃላትና ለትርጉም አስቸጋሪ የሆኑ ሐሳቦች የተደረደሩበት ባይሆን ይመረጣል። ለአድማጭም እንግዳ መሆን የለበትም፤ ለምሳሌ «የእግዚአብሔር ህላዌ በሁሉ ስፍራ» ከማለት ይልቅ «እግዚአብሔር በሁሉ ስፍራ አለ» ማለት ነገሩን ግልጽ ያደርገዋል።

ቀላል ሐረጎች አርእስቶችን ለማያያዝ ይረዳሉ፤ ሆኖም ከስብከቱ ሐሳብ ጋር የሚስማሙ መሆን አለባቸው። እንደ ሰባኪያን የእኛ ዓላማ ሰዎች አሰባበካችንን እንዲያስታውሱ ሳይሆን የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት እንዲገነዘቡ ማድረግ ነው። አንዳንድ ጊዜ ሦስት ወይም አራት ዋና ዋና ነጥቦችን አዘጋጅተን ከሆን እነዚህን ማስታወቅ አያስፈልገንም። ሁሉም ነገር የሚመሠረተው በስብከት አደረጃጀታችን ላይ ነው። ስብከት ስናዘጋጅ እንደ አስፈላጊነቱ መለዋወጥ አለብን።

## መረጃዎችን ደግሞ ለስብከት መጠቀም ስለመቻል

ስብከት ለማዘጋጀት የሚረዱንን ሐሳቦች ለመበሰብሰብ መጽሐፍ ቅዱስንና በእርሱ ላይ የተጻፉ መጻሕፍትን ስናነብ፥ ስናጠናና ስንመረምር እንደነበርን፥ በጥናታችን ወቅት ብዙ ጠቃሚ ሐሳቦችን ከጻፍን በኋላ በከፊል ለስብከት ተጠቅመንባቸው የቀሩትን ለወደፊቱ እንዲሆኑን ማስቀመጣችንን እናስታውሳለን። ስለዚህ ወደ ፊት ስብከት የምናቀርብ ከሆንን ቀደም ሲል ያዘጋጀነውን ስብከት እንደገና ስለማናቀርብ አዲስ ስብከት ስናዘጋጅ ባለፈው ጊዜ ያልተጠቀምንባቸውን ዋና ዋና ነጠቦች በማስገባት ቀደም ሲል የተጠቀምንበትን ማስታወሻ ማስቀመጥ እንችላለን። እነዚህን ማስታወሻዎች ለአንድ ጊዜ ልንጠቀምባቸው ካዘጋጀናቸውና በሚቀጥለው ጊዜ እንድንጠቀምባቸው ከፈለግን ዳግም ልንጽፋቸው ይገባል። ይህ ማስታወሻዎችን ዳግም የመጻፍ ልምድ አርትዖት በማድረግ ከመጽሐፍ ቅዱስ አተገባበር ጋር እንዲስማማ በማድረግ የምናዘጋጀው ስብከት በሐሳቡ የበሰለና ጊዜውን የጠበቀ ስለሚሆን ጥቅም አለው።

ምንም ዓይነት እበታ የሚባል፥ ከፍጸሜ የሚደርስ ጥናት የለንም። ስለዚህም የጻፍነውንም ሆነ የሰበክነውን ስብከት ዳግም ለማየት፥ ለማጥናትና ካስፈለገም ለመለወጥ ፈቃደኞች መሆን ይኖርብናል። ዕውቀታችን እያደገና የአድማጮችም ሁኔታ እየተለወጠ ሲሄድ የስብከቱን ይዘት እናሻሽል። አንዳንድ ስብከቶች አሰደናቂ ሊሆኑ ይችላሉ። ሆኖም ደጋግመን ካቀረብናቸው ይሰለቻሉ። ባጠቃላይ ከሰበክን በኋላ የትና መቼ እንደ ሰበክን ጽፈን ማስቀመጥ ይገባናል።

# ፮

## ተቀባዩን ዒላማ ያደረገ ስብከት

### የእግዚአብሔር ቃል እንጂ የእኛ ቃል አለመሆኑ

ስብከታችንን የፈለገውን ያህል ጥረት በማድረግ ድንቅ በሆነ ይዘትና ሐሳብ አዳብረንና አዘጋጅተን ለአድማጮች ብናቀርብው፥ ምን ጊዜም ከአዕምሯችን ውስጥ መጥፋት የሌለበት እውነት፥ የመልእክቱ መንፈሳዊ ኀይል የሚገኘው ከእኛ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ዘንድ መሆኑን ነው:: በእግዚአብሔር ላይ መደገፍ አለብን፤ በእርሱ ላይ መደገፋችንንም በማያቋርጥ ጸሎት መግለጽ ይኖርብናል::

ሐዋርያው ጳውሎስ በአንድ ወቅት ላይ መንፈሳዊ አገልግሎቱ ፍሬያማ ሊሆን የቻለበትን ምክንያት ለተሰሎንቄ ክርስቲያኖች ሲገልጽ፥ ለእነርሱ የሰበከው ስብከት ወደ እነርሱ የመጣው «... በኀይልና በመንፈስ ቅዱስ፥ በብዙም መረዳት እንጂ በቃል ብቻ ...» እንዳልሆን አስታውሷቸዋል፤ (1ተሰ. 1፥5):: እንደዚሁም በቆሮንቶስ ውስጥ ምንም እንኳን ስብከቱ እንደ ወትሮው በቃላቱና በአነጋገሩ የተዋጣለት ባይሆንም ፍሬያማ ነበር:: ሆኖም የቆሮንቶስ ሰዎች እምነት በእርሱ ስብከት አዋቂነት ላይ የተመሠረተ ሳይሆን በሚሰብከው የመልእክቱ እውነት ላይ መሆኑን ያውቅ ስለ ነበር ተስፋ አልቈረጠም:: እምነታቸው የተደገፈው በሰው ጥበብ ላይ ሳይሆን በእግዚአብሔር ኀይል ላይ ነበር፤ (1ቆሮ. 2፥1-5)::

እንደ ሰባክያን የእኛ ብቸኛ ሥልጣን የምንሰብከው ቃል ሥልጣን ነው፤ ኀይላችንም በእኛ ውስጥ ከሚሠራው ከእግዚአብሔር መንፈስ የተሰጠን ነው:: ኀይልን በውስጣችን ከሚሠራው ከእግዚአብሔር መንፈስ በጸሎት እናገኛለን::

ማድረግ ያለብንን በግልጽነት እናድርግ:: ሰዎች ግራ የሚጋቡበትንና ሊያዳምጡት የማይችሉትን እንዳንሰብክ እንጠንቀቅ:: በሌላ በኩልም ከፍተኛ ደረጃ ያለው ስብከት በማዘጋጀት አድማጮቻችን እንዲያደንቁን የማድረግ ዓላማ ሊኖረን አይገባም:: የስብከቱ ኀይል ያለው በሰባኪው ውስጥ ሳይሆን በቃሉ ውስጥ ነው:: ጳውሎስ «ነገር ግን የኀይሉ ታላቅነት ከእግዚአብሔር እንጂ ከእኛ እንዳይሆን ይህ መዝገብ በሸክላ ዕቃ ውስጥ አለን» ያለውን እናስተውል፤ (2ቆሮ. 4፥7)::

### ለቅዱሳት መጻሕፍት እውነተኛ ስለ መሆን

በአንድ በኩል ከሰው ልጅ የተፈጥሮ ግብዝነት ጋር ስንታገል በአንጻሩ ደግሞ አድማጮች መስማት የሚፈልጉትን መልእክት ከማዘጋጀት ፈተና ጋር

እንታገላለን:: መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛውን ቃል በመስበክ ፈንታ አድማጮችን ለማስደሰት ብቻ ስብከት የሚያቀርቡትን ሰዎች አዘውትሮ ያወግዛል፤ ሐሰተኞች ነቢያትም ይላቸዋል፤ (ኢሳ. 30፥10-11 ፤ 2ጢሞ. 4፥3):: እንዲህ ያሉ ሰዎች ለጊዜው ታዋቂዎች ይሆናሉ፤ በመጨረሻ ግን ራሳቸውንና የሚሰሟቸውን ሰዎች ይጐዳሉ፤ (1ነገ. 22፥13 ፤ ኤር. 5፥31 ፤ 23፥16-22):: በተቃራኒው ደግሞ ሰዎች ለመስማት ፈቃደኞች ቢሆኑም ባይሆኑም እውነተኞች የእግዚአብሔር መልእክተኞች ሊነገር የሚገባውን ይናገራሉ፤ (1ነገ. 22፥1 ፤ ኤር. 1፥17 ፤ ሚክ. 3፥8 ፤ 2ጢሞ 4፥2)::

ይህም በስብከታችን ውስጥ ከባድና ጎጂ ቃላትን እንናገር፥ የሰዎችን ስሜት እንንካ ማለት አይደለም:: በቀጥታ ስሜትን መግለጽ እብሪተኝነት አይደለም:: ጌታ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንገድ በቀጥታ በማስተማር፥ ስለ ሰዎች አስተያየትና ሥልጣን ሳይጨነቅ እውነቱን ብቻ በመናገር የታወቀ ነበር፤ (ማር. 12፥14):: እንዲያውም በቃላቱና በባሕርዩ ጸጋን የተሞላና የሚደነቅም ነበር፤ (ሉቃ. 4፥22 ፤ ዮሐ. 7፥46)::

የቤተ ክርስቲያን አማኞች ልዩ ልዩ ፍላጎቶች አሏቸው:: እልኸኞችን መገሠጽ፥ ሰነፎችን ማስጠንቀቅ፥ ዐይን አፋሮችን ማበረታታት፥ ያዘኑትን ማጽናናት ያስፈልጋል፤ (ሮሜ 12፥7-8 ፤ 1ተሰ. 5፥14 ፤ 2ጢሞ. 2፥24-26):: በምንሰብከው ማንኛውም መልእክት ውስጥ የእግዚአብሔርን ቃል መተርጐምና በተግባር ላይ ማዋል በምንችልበት ደረጃ ላይ ታማኞች ሆነን መገኘት አለብን:: የመጽሐፍ ቅዱስን መጽሐፍ፥ በሌላ አቅጣጫ ለውጠን ለመጠቀም ብለን ጸሐፊው ያላለውን እንዳለ በማስመሰል ቀጥተኛውን ቃል ወደ ሌላ መጠምዘዝ ፈጽሞ የለብንም:: የእግዚአብሔርን ቃል ከሐሰት ጋር ማቀላቀልና ከትርጕሙ ውጪ ማጣመም አይገባንም:: ይልቁንም እውነትን በግልጽ እየተናገርን በእግዚአብሔር ፊት በሰው ሁሉ ኅሊና ተቀባይነት እንዲኖረን መጣር አለብን፤ (2ቆሮ. 4፥2)::

በጉባኤው ውስጥ የተለያየ አመለካከት ያላቸው ሰዎች መኖራቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት ስብከታችን ሚዛናዊ የሆነ ዝግጅት እንዲኖረው ለማድረግ የመጽሐፍ ቅዱስን ክፍሎች በሙሉ ለመዳሰስ የሚያስችል ዓመታዊ መርሐ ግብር ማውጣት አለብን:: ይህን ጉዳይ በተመለከተ በምዕራፍ ዐሥራ ሁለት ላይ በዝርዝር እንነጋገርበታለን:: እዚህ ላይ ግን ማንሣት የምንፈልገው፥ መርሐ ግብር ማዘጋጀቱ የሚጠቅመን መላውን መጽሐፍ ቅዱስ ለማጥናት በምናደርገው እንቅስቃሴ ብዙ ፀይነት ርእሶችን ለመዳሰስ ስለሚያግዘን ነው:: ይህን በምናደርግበት ጊዜ የቤተ ክርስቲያንን ፍላጎት እያሟላን፥ በአኳያው ለተለዩ አድማጮች ብቻ ስብከት የማዘጋጀቱን አጕል ልምድ የማስወገድ ዕድል እናገኛለን:: እንደዚሁም አንድን መጽሐፍ ስናብራራ በተለይ በስብከት ዝግጅት ጊዜ ማብራራት የሚያዳግተንን በዚህ ወቅት ማብራራት እንችላለን::

## ከአድማጮች አስተሳሰብ አኳያ

ወደ መድረኩ ስንወጣ ስለምንሰብከው ስብከት የምናውቅና ስሜታችንም ዘና ያለ ሲሆን፥ በአንጻሩ አድማጮቻችን ስለሚሰበከው ክፍል ሳያውቁ ቀዝቃዛ ስሜት ይዘው ይመጣሉ። የእኛ አዕምሮ ባጠናናቸው ነገሮች የተሞላ ሆኖ ሳለ፥ በአንጻሩ የአድማጮቻችን አዕምሮ ደግሞ የተዘጋጀ አይደለም። ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲመጡ እኛ ለስብከት የሚሆኑትን ርእሶች አጥንተን እንደ መጣን ዐይነት አይደሉም። በእኛ አዕምሮ ውስጥ ግልጽ ሆኖ የተረጋጋውን ነገር መመልከት አይችሉም። ስለዚህ ወደ መድረኩ ከወጣን በኋላ ስለምንሰብከው ርእሰ ጉዳይና ስለ አካሄዱ የመንደርደሪያ ሐሳብ መስጠት ይጠበቅብናል።

በተጨማሪም ስብከታችንን ባዘጋጀንበት ጊዜ በአዕምሯችን ውስጥ ጥያቄዎች ተነሥተውብን ከሆነ በምንሰብክበት ወቅትም በአድማጮቻችን አዕምሮ ውስጥ ጥያቄዎች ሊነሡ እንደሚችሉ እርግጠኞች ልንሆን ይገባል። በስብከታችን መሐል ሊነሡ ስለሚችሉ ክርክሮችና ተቃውሞዎች ልናስብና መልስ ልንሰጥ ይገባናል። ለምሳሌ :- «አሁን ምናልባት ... ትሉ ይሆናል» የሚልና ሌላም ግምታዊ ማብራሪያ ስጥተንበት እንቀጥላለን።

ጳውሎስ ካነሣቸው ጥያቄዎች መካከል ፦ «እንግዲህ የአይሁዳዊ ብልጫው ምንድር ነው? ወይስ የመገረዝ ጥቅሙ ምንድር ነው? በሁሉ ነገር ብዙ ነው»፤ (ሮሜ 3፥1-2)። «የማያምኑ ቢኖሩ አለማመናቸው የእግዚአብሔርን ታማኝነት ያስቀራልን? እንዲህ አይሁን፤ ...»፤ (ሮሜ 3፥3-4)። «እንግዲህ ምን እንላለን? ጸጋ እንዲበዛ በኀጢአት ጸንተን እንኑርን? አይደለም። ለኀጢአት የሞትን እኛ ወደ ፊት እንዴት አድርገን በእርሱ እንኖራለን? ... » (ሮሜ 6፥1-3) የሚሉ ይገኙበታል።

በዘመነ ብሉይ የነበረው፥ ሰባኪው ሚልክያስ አድማጮቹ በሠሩት ጥፋት ሲገሥጻቸው የተናገራቸው በተመሳሳይ ሁኔታ ነበር። በመጀመሪያ ስህተታቸውን ያመለክታቸውና ከዚያ ቀጥሎ የእነርሱን መልስ ይነግራቸዋል፤ (ሚል. 1፥6)። ነቢዩ በእግዚአብሔር ፊንታ ሆኖ፥ ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ስም በማቃለላቸው ይከሳቸዋል? ሕዝቡም የማስተባበል ምጸት ባለው አነጋገር መልሰው፥ «ስምህን ያቃለልነው እንዴት ነው?» ይላሉ። ሚልክያስም እግዚአብሔርን ወክሎ ሲመልስ፥ «በመሠውያዬ ላይ ርኩስ እንጀራ ታቀርባላችሁ»፤ ይላቸዋል። እነርሱም ቅሬታ ባለው አነጋገር፥ «ያረከስንህ በምንድር ነው?» ብለው በጠየቁት ጊዜ፥ ስህተታቸውን በሚቀጥሉት ጥቅሶች በዝርዝር ያስረዳቸዋል።

ሚልክያስ ስህተታቸውን እየነቀሰ ማስረዳቱን ይቀጥላል። ለምሳሌ:- በምዕራፍ 2፥17 ላይ «እግዚአብሔርን በቃላችሁ አታክታችኋል» ብሎ ሲናገራቸው ሕዝቡ ደግሞ «ያታከትነው በምንድር ነው?» ይላሉ። ሚልክያስም መልሶ፥ «ክፉን የሚያደርግ ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ መልካም ነው፤ እርሱም በእነርሱ ደስ

ይለዋል፤ ወይስ የፍርድ አምላክ ወዴት አለ? በማለታችሁ ነው»፤ ይላቸዋል። ከዚያም ንግግሩን በማስረዘም በሚቀጥለው ምዕራፍ ይነግራቸዋል። እኛም እንደ ሰባኪነታችን እንደዚህ ያሉ ነጥቦችን ብናነሣ የአድማጮቻችንን ልብ ልንስብ ከመቻላችንም በላይ ለስብከቶቻችንም መልካም ግምት ያሰጣል።

## የአድማጮቻችን ስብጥር

አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንዴት ከየዕለቱ የሕይወት አኗኗር ጋር እንደሚስማማና በተግባር ላይ ሊውል እንደሚችል ልናስተውል ይገባናል፤ በአንጻሩ ሌሎች ሰዎች ይህን በፍጥነት ሊገነዘቡት አይችሉም ይሆናል። ምክንያቱም የአንዱ ሰው ሁኔታ ከሌላው ይለያል፤ ለአንዱ ሰው የሚያስፈልገው ለሌላው ላያስፈልግ ይችላል። አድማጮቻችን አብዛኛውን ጊዜ የወጣቶችና የሽማግሌዎች÷ የወንዶችና የሴቶች÷ ያገቡና ያላገቡ÷ የነጋዴዎችና የተማሪዎች÷ በጥቅሉ የብዙ ሕዝብ ስብጥር ናቸው። ስለዚህ የስብከት ዝግጅታችን የተወሰኑ ጥቂት የኅብረተሰብ ክፍሎችን ብቻ በማሰብ እንዳይሆን መጠንቀቅ አለብን።

ሌላው ድግሞ ሁሉንም ሰው በአንድ ጐራ የሚፈርጅ ስብከት ከማድረግ መጠንቀቅ ይበጃል። ለምሳሌ አድማጩ በተሰበሰበበት ወጣቱን በጅምላ የሚያብጠለጥልና የሚገሥጽ ስብከት ብንሰብክ÷ በዚህ ዕድሜ ውስጥ የሌሉትን አድማጮች ግራ ያጋባቸዋል፤ ደግሞም ለእነርሱ ሊነገር የማይገባውን ነገር ይሰማሉ። ሁሉን አቀፍ የምስጋና ቃልም ራስን በውሸት ከማርካት አኳያ ከትዝብት ላይ ስለሚጥል ጠቃሚነት የለውም።:

ሁለት ሰዎች አንድ ዐይነት ሊሆኑ ስለማይችሉ በተግባር ላይ ስለሚውሉና ሊታረሙ ስለሚገባቸው ሁኔዎች ቃላትን በጥንቃቄ መምረጥ አለብን። ለተለያዩ ሰዎች የምናቀርባቸው ማብራሪያዎች ወይም ጥያቄዎች በቃል አስካካቸው በተለያዩ ግለሰቦች የተለያየ ደረጃ ያላቸው ምላሾችን ሊያገኙ ይገባል። ሰዎች የተለያዩ መልሶችን ሊሰጡ ስለሚችሉባቸው መንገዶች እንዲያስቡ መርዳት ያስፈልጋል። ጌታ ኢየሱስ በጌታቸው ላይ ስለ ዐመፁ የወይን ስፍራ ገበሬዎች ምሳሌ በተናገረ ጊዜ አድማጮቹ በምሳሌው ስለተሰጠው ትምህርት ትርጉምና ከሕይወታቸውም ጋር ስላለው ተዛምዶ እንዲያሰላስሉ አድርጎ ይናገር ነበር። እንደተባለው በጥሞና ሰምተውት ስለ ነበረ ጌታ የተናገረው ምሳሌ እነርሱን÷ ራሳቸውን መገሠጽ እንደ ነበረ ተገነዘቡ፤ (ማር. 12÷12)።

ጌታ ኢየሱስ የደቀ መዛሙርቱን እግር ባጠበ ጊዜ ያስተማራቸው ሊከተሉት የሚገባቸውን የትሕትና ትምህርት ነበር። በተግባር ላይ የማዋሉ ጉዳይ ከሰው ሰው የሚለያይ ቢሆንም ለእነርሱ የሚገባቸውን ትምህርት ሰጥቷቸዋል፤ (ዮሐ 13÷12-17)።. እኛም ሌሎችን ስለ ማገልገል ብንሰብክ÷ የሰዎችን ደረጃ÷ ምኞት ወይም ነጻነት ከግምት ውስጥ ሳናስገባ በቀጥታ ራሳችንን እንዴት አድርገን

መሥዋዕት ማድረግ እንደምንችል በስብከታችን ውስጥ ተጨባጭ የሆነ ምሳሌ ማሳየት እንችላለን፤ በተግባር ላይ አውሉ ውጤት በማምጣት ረገድ ግን ከእያንዳንዱ ሰው ልንጠብቅ እንችልም:: ሰዎች የየራሳቸውን ኀላፊነት እንዲወጡ ማበረታታት አለብን:: ኢየሱስ የርኅሩኅን ሳምራዊ ታሪክ ለሕግ ዐዋቂው ሰው «አንተም ሂድና እንዲሁ አድርግ» አለው፤ (ሉቃ. 10÷29÷37):: ለጊዜው ለሰውየው የታየው አንድ ነገር ማድረግ ነበር፤ ኋላ ግን ሌሎችን ማገልገል ሆኖ አገኘው::

ሌላው ልናስተውለው የሚገባ ቁም ነገር በንግግራችን ውስጥ አንድን ነገር አጉልቶ የሚያስቀምጥ ንግግር እንዳናደርግ ነው:: ለምሳሌ ጻድቃን ሁልጊዜ ይበለጽጋሉ፤ ጸሎት ሁልጊዜ መልስ ያገኛል፤ ወይም ሥቃይ ሁልጊዜ የግል ኀጢአት ውጤት ነው፤ ብለን ማረጋገጥ አንችልም:: የሰጠነው ምክንያት እውነት ሆኖ ካላገኙት ሰዎች ለስብከታችን ከበሬታ አይሰጡም፤ እንዲያውም ያቃልሉናል::

እንዲሁም ብዙ ስለማናውቀው ነገር ለማብራራት በምንነሣበት ጊዜ ዝግጅታችን በቂ ማስረጃና ማብራሪያ በውስጡ ስለመያዙ አስቀድመን መመርመር አለብን:: ለምሳሌ:- ስለ እርሻ ሙያ የምናውቀው በመጠኑ ቢሆንም ጠቃሚ መረጃ የሚሰጠን ታሪክ በጆሮ ሰምተን ይሆናል:: እንግዲህ እኛ በምናቀርበው ትምህርት ውስጥ የምንጠቀምበት ማብራሪያ ሊረዳን ቢችልም በንግግራችን ላይ ስለ እርሻ ሙያ እውነት ያልሆነ ነገር ብንናገር በአድማጮቻችን መካከል ባሉ ገበሬዎች ዘንድ ውሸታሞች ተብለን እንነቀፋለን::

## ከአድማጭ ጋር ራስን ማሳተፍ

በአገልግሎት ጊዜ ከአድማጭ ጋር ከሆንን÷ በአገልግሎቱ ውስጥ ሙሉ ተሳታፊዎች ለመሆናችን እርግጠኞች ልንሆን ይገባል:: በሚካሄደው አገልግሎት ውስጥ ለምሳሌ በዝማሬ÷ በጸሎት÷ በምስክርነት እንዲሁም በማስታወቂያ ውስጥ ተሳታፊነታችንን ብናሳይ የእኛ የማገልገል ተራ ሲደርስ አድማጭ ደግሞ በአጸፋው በምናደርገው አገልግሎት ላይ ልባዊ ተሳትፎውን ይገልጻል::

በአገልግሎቱ ውስጥ ተሳታፊዎች መሆናችን እንድንረጋጋ ይረዳናል፤ መንፈሳችን በተረጋጋ ቊጥር ደግሞ ነገሮች በሰከነ ሁኔታ ይሄዱልናል:: አንዳንድ ሰባክያን በመጨረሻው ሰዓት የስብከት ማስታወሻቸውን ማንበብ÷ በመድረክ ላይ የቡድን ጸሎት መጸለይ አይፈልጉም:: ከቤታችን ከመውጣታችን በፊት የስብከት ማስታወሻዎቻችንን ማስተካከልና መጸለይ ከዚያም ራሳችንን ለእግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ ማስረከብ ተገቢ ነው:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የዕለቱ ሥነ ሥርዓት ሲካሄድ÷ ሐሳባችንን የሚበትን÷ ስሜታችንን የሚጻረር ሁኔታ እንዳይከሰትም መጠንቀቅና ራሳችንን ማረጋጋት ይኖርብናል:: ደግሞም ወደ ስብከቱ አዳራሽ ከመግባታችን በፊት ባለው ሰዓት÷ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወዳለው ንባብ ክፍል

ገብተን ዝግጅታችንን መመልከትና ማደራጀት አለብን። አንድ ጊዜ ወደ መድረኩ ወጥተን መናገር ከጀመርን የተመሰቃቀሉ ማስታወሻዎችን ማስተካከል አንችልም።

አንዳንድ ሰባኪዎች የአድማጮችን ልብ ለመሳብ ጥበባዊ ቀልዶችን ወይም አባባሎችን ይጠቀማሉ። ነገር ግን እንዲህ ያሉትን የማነቃቂያ ዘዴዎች በጣም አስፈላጊዎች እንደ ሆኑ አድርገን ማሰብም የለብንም። በተለይ ከእኛ የስብከት ዘዴ ጋር በተለምዶ የምናደርገው ስልት ካልሆነ በስተቀር ብናስቀረው መልካም ነው። የምናቀርበውን ርእሰ ጉዳይ አስበንበት ከሰበክነው፥ ከምንሰብከው ቃል የሚወጣው ፍሬ ነገር ራሱ የአድማጮችን ስሜት ሊቈጣጠር ይችላል። ጌታ ኢየሱስ በኤማሁስ ጉዞ ላይ ለሁለት ደቀ መዛሙርት ቅዱሳት መጻሕፍትን ባብራራላቸው ጊዜ ልባቸው ተነካ፤ (ሉቃ. 24፥27፥32)። ሌሎች ሰዎች ስለ እነርሱ ስለሚያስቡ ሰዎች ሐሳብ ያድርባቸዋል፤ ይግባባሉም፤ (2ቆሮ. 9፥2)። ደግሞም አንድ መልእክት ለማቅረብ ምንም ያህል መስዋዕትነት ያስከፍላቸው፥ ስለሚያቀርቡት መልእክት ራሳቸው ከበሬታ ከሰጡት አድማጮቻቸውም አጸፋውን ከበሬታ ይሰጧቸዋል፤ (ሐዋ. 20፥31)።

## ሕይወት ያለው ይዘት

መጽሐፍ ቅዱስን በጥረት አስደሳች አድርጎ በማቅረብ የአድማጩን ቀልብ ለመሳብ ተብሎ አላስፈላጊ ነገር መጨመር ወይም ጣልቃ ማስገባት አያስፈልግም። አንዳንድ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን የሚጠሉት ወይም የሚቃወሙት፥ መጽሐፍ ቅዱስ በራሱ የማይስብ ወይንም የማይጥም ነገር ያለበት መጽሐፍ ሁኖ ሳይሆን በአጠቃላይ ክርስቲያኖች በተለይም ሰባኪዎች ስለ መጽሐፍ ቅዱስ እውነቱን ጥርት ባለ መንገድ ማቅረብ ባለመቻላቸው ብቻ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን ያለው መጽሐፍ መሆኑን ተረድተን የሚገባውን ክብር ልንሰጠው ያስፈልጋል፤ እንዲህ ሲባልም ደግሞ ግልጽ ባልሆነ ቋንቋ አክብረን በንባብ እናቀርበዋለን ማለትም አይደለም። ይህን በተመለከተ ጥንቃቄ ካላደረግን በስተቀር፥ መጽሐፍ ቅዱስን አክብሮት አይሉት ሌላ በሆነ ስሜት ተይዘን በማንበብ ለሕይወታችን ጠቃሚ መሆኑን ሳንቀምስና ሳንረዳ እንቀራለን።

ለመጽሐፍ ቅዱስ ተገቢውን ክብር እንስጥ ሲባል፥ መሠረተ ሐሳቡን በትክክል ተገንዝበን እናብራራ ማለት ነው። ይህን ስናደርግ አንዳንድ ጊዜ በጠንካራ ቃላት ሲናገር፥ በዓለማዊ ማስረጃዎች ሲጠቀም፥ ለትምህርት አጠያያቂ የሆኑ ታሪኮችን ይዞ እናገኘዋለን። ጳውሎስ አገልግሎቱን ለማበላሸት የሞከሩትን በጥንካራ ቃላት ይገሥጽ ነበር፤ (2ቆሮ. 11፥19-21 ፤ 12፥11-13 ፥ 20-21 ፤ ገላ. 1፥8-10 ፤ 5፥12) ፤ ነቢያት የሕዝብን አለመታመን ከምንዝርናና ከሌሎች ልቅ የግብረ ሥጋ ግንኙነቶች ጋር አመሳስለው ሲናገሩ በዓለማዊ ተምሳሌቶች ይጠቀሙ ነበር፤ (ሕዝ. 23፥1-4፥ 20-21፤ ሆሴዕ 2፥1-5) ፤ የሕዝብን ዐመፅና ነውር ይፋ በሚያወጡ ታሪኮች ይገልጹ ነበር፤ (ዘፍ. 24፥1-31 ፤ መሳ. 19፥1-21 ፥ 25)።

ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚያስፈሩ ክፍሎችን በመናገር አድማጮችን ሥጋት ላይ መጣል የለብንም፤ በእንጻሩም እነዚህን ክፍሎች በማስወገድ ወይም እውነት ያልሆኑ ትርጉሞችን በመስጠት አድማጮቻችንን ማደናገር አይገባም። ቀደምት እንባብያን እንብበው የተገነዘቡትን ቃል በቀላሉ ማብራራት ይኖርብናል። ይህን አድርገን ኀላፊነታችንን በምንወጣበት ጊዜ፥ መጽሐፍ ቀዱስ ሕያው የሆነ መልእክት እንዳለው እናረጋግጣለን። ስሜትን የሚቀሰቅስ ለማድረግ ብለን የራሳችንን ታሪክ ልንቀላለቅልበት ተገቢ አይደለም። እኛ ጸሐፊው መልእክቱን በምን አኳኋን እንዳቀረበ በአዕምሯችን ማሰብ፥ ከዚያም የደራሲውን ተልእኮ በትክክል ለአድማጮች መግለጽ አለብን።

የመጽሐፍ ቅዱስን ክፍል ገላጭ ከሆነና ደረጃውን ከጠበቀ ዘመናዊ ሐሳብ ጋር በማዛመድ አጒልተን ማቅረብ እንችላለን። እግዚአብሔር በነቢዩ አሞጽ አፍ «እነሆ፥ ነዶ የተሞላች ሠረገላ እንደምትደቀድቅ እንዲሁ አደቀድቃችኋለሁ» ይላል፤ (አሞጽ 2፥13)። ይህንኑ ቃል በጊዜያችን ካለ ምሳሌ ጋር አያይዘን ለመግለጽ ብንፈልግ ዐሥር ቶን ጭነት የተሸከመ መኪና እንደሚያደቅ እግዚአብሔር እንዲሁ ያደቅቃችኋል ማለት እንችላል።

እግዚአብሔር ኢሳይያስን ትልቅ ሰሌን ወስደህ ለሕዝቡ መልእክት ጻፍ ብሎ ያዘዘውን፣ ከዛሬው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ብናመዛዝነውና ለመተግበር ብንፈልግ፥ ልክ ከቤቱ ውጪ ጥቁር ሰሌዳውን አስቀምጦ የታዘዘውን መልእክት እንዲጽፍ አድርገን እንቈጥረዋለን፤ (ኢሳ. 8፥1)። በጠመኔ በሰሌዳው ላይ እንደሚጽፍ በተመሳሳይ ሁኔታ ነቢዩ ዕንባቆም በጊዜው የታዘዘው፥ አላፊ አግዳሚው ሊያነበው እንዲችል መልእክቱን በትላልቅ ፊደሎች፥ በሰሌዳ ላይ እንዲጽፍ ነው፤ (ዕን. 2፥2)። ይህን ከዛሬው ሁኔታ ጋር ብናመዛዝነው፥ አንድ ሞተር ሳይከል የሚነዳ ሰው በቀላሉ አንብቦት ሊያልፍ ከሚችለው ከመንገድ ዳር ማስታወቂያ ጽሑፍ ጋር እናመሳስለው ይሆናል። ወይም ጋዜጣ ከሚሸጥበት መደብር ውጪ የሚያልፉ አንባቢዎችን ልብ ለመሳብ የተቀመጡ አርእስተ ዜናዎችን ይመስላል።

እነዚህን ሥዕላዊ ቃላት ለመግለጽ አንድ ወይም ሁለት ዐረፍተ ነገሮች ብቻ ያስፈልጉናል፤ የሚወስዱትም የስብከታችንን ጥቂቱን ጊዜ ብቻ ነው፤ ቢሆንም የምንሰብከውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አድማጮች ከልብ እንዲያዳምጡ ያደርጓቸዋል። ይልቁንም መጽሐፍ ቅዱስን በተጻፈበት ሁኔታ እንዲገነዘቡት ከማድረግም በላይ ከዛሬው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እንዲያዛምዱት ይረዷቸዋል።

እያሌ የብሉይ ኪዳን ነቢያት በዘመናቸው የነበረው ጭቆና፥ ለምሳሌ እጅ መንሻ የሚቀበሉ ፈራጆችን (ሚክ. 7፥3)፥ ድኻውን ወደ ባሰ ድኽነት የሚከቱ አራጣ አበዳሪዎችን (አሞጽ 2:6-8)፥ ሥልጣንን ለጥቅማቸው የሚያውሉ ፖለቲከኞችን (ኢሳ. 22፥15-19)፥ ምስኪን ዜጎችን የሚያጭበረብሩትን (አሞጽ 8፥5-6)፥ ውብ ቤቶችን ለራሳቸው በመሥራት ሕዝባቸውን የሚያፈልሱትን (ኤር.

22÷13-18)÷ ድኻውን የሚበዘብዙ ባለጸጎችን (አሞጽ 5÷11-13) በድፍረት ይቃወሙ ነበር:: የዛሬዎቹ አንባቢዎች ይህንን ለማድረግ ይቸገራሉ::

## ብሩህ አቅጣጫን ማየት

ምንም እንኳን የመጽሐፍ ቅዱስ ሰባኪዎች በቀጥታና ፊት ለፊት የሚናገሩ ቢሆኑም ነገርን የሚያንዛዙ÷ ፈገግታን የማያውቁ ዐይነት ሰዎች አድርገን መመልከት የለብንም:: በአንጻሩ አንዳንድ ጊዜ ለዛ ያለው ጨዋታ ሲጫወቱ እናገኛቸዋለን:: በሚጽፉበትም ጊዜ እንደማንኛውም ሰው የተለያዩ ሰዎችን የተለመደ የአነጋገር ባሕርይ አጋኖ የሚናገረውን ምጸትን÷ አሽሙርንና የመሳሰሉትን በጽሑፋቸው ውስጥ ይገልጻሉ::

በአሞጽ ዘመን የነበሩ እስራኤላውያን እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን አጥፍቶ ድልን እንዲያጐናጽፋቸው ፈልገው ስለ ነበር የጌታን ቀን በተስፋ ይጠባበቁ ነበር:: አሞጽ ግን ይህን የተሳሳተ አመለካከታቸውን ለማረም ሲል እግዚአብሔር ፍርድን በሚልክበት ጊዜ በክፉዎች እስራኤላውያንም ጭምር እንደ ሆነ አረጋገጠላቸው:: ከዚያ ፍርድ የሚያመልጥ ማንም አይኖርም:: ነቢዩ ስለ እግዚአብሔር ቀን ሲናገርና ሲያስጠነቅቃቸው «ይህ ቀን አንድ ሰው ከአንበሳ ሲሸሽ ድብ እንደሚያጋጥመው÷ ወደ ቤቱም ገብቶ እጁን በግድግዳው ላይ ሲያሳርፍ እባብ እንደሚነድፈው ነው» ይላል፤ (አሞጽ 5÷18-19):: የጌታን ቀን ለማስረዳት የተጠቀመበት ምሳሌ አጭርና ግልጽ ነው፤ ነገር ግን ይህን ቃል ለአድማጮች ብናነብላቸውና ባናብራራላቸው ግልጽ ላይሆንላቸው ይችላል::

የአሞጽን ንግግር ሥዕላዊ ሐሳብ ከተገነዘብን አድማጮቻችን ይህንኑ ሐሳብ ግልጽ በሆነ መንገድ እንዲሰሙት መርዳት ይገባናል:: ይህን ምሳሌያዊ ትምህርት ስናብራራም እንዲህ እንላለን፤ አንድ በገጠር ያለ ሰው በድንገት አንበሳ ሊሰብረው ከተፍ ይልበታል፤ ይህ የደነገጠ ሰው ከአንበሳው ለማምለጥ ሲል እየጮኸ÷ እጆቹን እያወናጨፈ÷ እየዘለለ÷ ሕይወቱን ለማዳን ይፈተለካል:: በወቅቱ የሚታየው ሁሉ ከሚጐዳው የዱር እንስሳ ለማምለጥ ነው:: በመጨረሻም አውሬው ተስፋ ይቈርጥና ማሳደዱን ይተዋል:: የሚሸሸው ሰውየም በተአምር በአንበሳው ከመበላት ይተርፋል:: ነገር ግን ከዚህ አሳዳጁ ድኖና ድካሙ ተግ ብሎለት እያለ÷ ከሌላ አቅጣጫ ድብ እየተንደረደረ ሲመጣበት ይመለከታል::

ይህ ምስኪን ሰው አሁን ደግሞ ድብ ያባርረዋል፤ እርሱም እጆቹን እያወናጨፈ÷ እየጮኸና እየዘለለ ለማምለጥ ይሮጣል:: እንደገና ያሁኑ ሐሳቡም ከሚበላው አውሬ ለማምለጥ ነው:: በዚህ ጊዜ ከፊት ለፊቱ ቤት ያይና ተንደርድሮ ወደዚህ ቤት ውስጥ ገብቶ በሩን ግጥም አድርጐ በመዝጋት በድብ ከመበላት ያመልጣል:: አሁንም በተአምር በአውሬ ከመበላት መዳኑን ግድግዳ ተደግፎ በማሰብ ላይ ነው:: ግን ይባስ ብሎ ከየት እንደመጣ ያላየው እባብ

ይነድፈዋል:: በጊዜው የአሞጽ የማስጠንቀቂያ መልእክት የሰሚዎቹን ልብ እንደሳበና ተደማጭነትን እንዳገኘ ሁሉ የእኛም መልእክት የአድማጮቻንን ትኩረት መሳብ አለበት:: የመልእክቱ ነጥብ ወይም ተልእኮ ከእግዚአብሔር የፍርድ ቀን የሚያመልጥ አንድም ሰው ሊኖር አይችልም የሚል ነው::

## ሌሎች ምሳሌዎች

ሌላው ልብን የሚነካ ማስጠንቀቂያ በኢዮብ መጽሐፍ መጨረሻ ክፍል ላይ እግዚአብሔር በግልጽ የተናገረው የተግሣጽ ቃል ነው:: ይኸውም ኢዮብ የሞራል ሕግን ሊጠብቅ ካለመቻሉም በላይ የተፈጥሮንና የግዙፉን ዓለም ሥርዓት ለመቈጣጠር የማይችል መሆኑን ያስገነዝበዋል:: እግዚአብሔር ይህንን ድካሙን በግልጽ ሲነግረው የአራዊት ዓለም እንኳ ከኢዮብ ዐቅምና ቍጥጥር ውጪ መሆኑን ይነግረዋል:: ለምሳሌ ስለ አዞ እናስብ:: ኢዮብ ብልሀተኛ ከሆነ ዐሣ በመንጠቆ እንደሚይዝ ሁሉ አንድ አዞ ሊይዝ ይችላል፤ ከዚያም ለማዳ ሊያደርገው ይጥራል:: እናም አዞው እንዲናገር ማለማመድ እንዲሁም አንዳንድ ልዩ የሆኑ አስደናቂ ነገሮችን እየሠራ እንዲያሳይ ለማድረግ ይሞክር ይሆናል:: ሴቶች ልጆቹም በአዞው አፍንጫ ውስጥ መሰንጊያ ሰክተው ልክ እንደ ውሻቸው ሸርሸር ይዘውት ለመውጣት ይሞክራሉ፤ (ኢዮብ 41:1-5) ትረካው በዚህ ሁኔታ ይቀጥላል:: በተገለጸው ክፍል ውስጥ የሚያስገርም ሁኔታ ይታያል፤ ታዲያ ይህንን ሁኔታ ማብራሪያዊ ስብከታችን ሊገልጸው ይገባል::

በኢየሱስ ንግግር ውስጥም በተመሳሳይ ሁኔታ ፈገግ ሊያደርጉን የሚችሉ ቃላት አሉ:: ለምሳሌ «ትንኟን የምታጠሩ፥ ግመልን የምትውጡ» (ማቴ. 23:24) የሚለው አነጋገር የሚያሳገርም ነው:: የግመሉ አንገት ወደ ሰውዬው ጉሮሮ ሊገባ ሲተናነቀው፥ ከእርሱ የባሰው ደግሞ የግመሉ ሻኛ ከውጭ ሲታይ፥ አያስገርምም! የግመሉ ቀሪው አካል ሌላው አደጋ ነው::

ሌላው ምሳሌ - ከአዝሙድ፥ ከከሙንና ከእንስላል ዐሥራት እየተቀበሉ የበለጠ ግምት የሚሰጣቸውን ድርጊቶች ከሚፈጽሙ ሰዎች የተነገረው ነው:: እርግጥ ስለተዘረዘሩት ቅመሞች ብዙ ሰው ላያውቅ ይችላል:: እነዚህ ሰዎች ከያዙት ሩዝ ዐሥር ዐሥሩን እየቈጠሩ ወደ ጎን ያስቀምጣሉ:: ከዚያም በዚያ መጠን የሚበሉትን ዐሥራት ይተምናሉ:: (ማቴ. 23:23) በዚህ ተምሳሌታዊ አነጋገር ውስጥ ስለተገለጸው መልእክት በጥብቅ ማሰብ አለብን:: ይህን ስናደርግ በመልእክቱ ውስጥ ፈገግ የሚያሰኙ ሁኔታዎችን በተናጋሪው ቃላት እናጤናለን::

## ቃላትን በጥንቃቄ መጠቀም

ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን መልእክቶች የመሰሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዙ ስፍራዎች ይገኛሉ፤ ሆኖም እንዲህ ያሉትን ክፍሎች ስናነብና መንፈሳዊ

ተልእኳቸው ሲገባን፥ ሌላውን ቀላል መልእክት ደግሞ አናስተውልም:: በምናነብበት ጊዜ ዘና ማለት አለብን:: ያኔ ጸሐፊው ያንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በምን ሁኔታ እንደ ገለጸው ግራ ቀኝ ትርጉሙን ማስተዋል እንችላለን፤ ከዚያም በአዕምሯችን ሥዕላዊ ቃላትን መቅረጽና አድማጮቻችን በስፍራው እንዳሉ ቈጥረው፥ የሚሰሙትን በዐይነ ኅሊና እያዩ እንዲያዳምጡት እናደርጋለን::

ነቢዩ ሚልክያስ፥ ስለ መሥዋዕት አቀራረብ (ሚል. 1፥8) አዝኖ የተናገረውን የምናብራራ ከሆንን አድማጮች በአዕምሯቸው ውስጥ በዐይነ ኅሊና ስለው ሊመለከቱ በሚችሉበት ሁኔታ አብራርተን ማቅረብ አለብን:: መሥዋዕት አቅራቢው ሰው አንካሳ የሆነውን፥ በሽተኛውን፥ ጅራተ ቈራጣውን፥ አንድ ጆሮ የሌለውን እንስሳ ይዞ ሲመጣ በዐይነ ኅሊናቸው ሥዕሉን ሊመለከቱ እንዲችሉ ማድረግ ይኖርብናል:: ምናልባትም አንድ እንስሳ ይዞ የሚመጣው ሰው «ኧሁ!» ሲል ያስባል፤ «ለማንኛውም ለሞት ነው ይዤው የምሄደው፤ በመሠዊያው ላይ ልረድና ልረፍ፤ ቢያንስ ለመሥዋዕት የመቅረብ ዕድል ይኑረው»፤ ይል ይሆናል::

ሕዝቡ የማይገባ መሥዋዕት ለእግዚአብሔር ስለሚያቀርቡ የነቢዩ የሚልክያስ ምላሽ ተግሣጽ የተሞላ ነው:: ለፋርሱ አገረ ገዥ «ክቡር አገረ ገዥ ሆይ! የማንፈልገውን በሽተኛ፥ የሸተተ እንስሳ እነሆ አምጥተንልሃል፤ በዚህ ደስ እንደሚልህ እርግጠኞች ነን፤ መልካም ልደት ይሁንልህ» ብለው ቢሰጡት የገዢ መልስ ምን ይሆናል? የእግዚአብሔርም ሕዝብ በሰዎች ላይ የማያደርጉትን ነውር እየፈጸሙበት ከእርሱ ግን መልካሙን ይሻሉ::

ያዳመጥነውን ትምህርት ተልእኮ የራሳችን አድርገን እንድንቀበለው መግለጽ ያስፈልገናል:: መልእክቱን ለመናገር ብዙ ምሳሌያዊ ማስረጃዎችን አንሻም፤ ክፍሉን እንዳለ፥ መሠረቱን ሳናናጋ ማብራራትና የሕይወት ጥቅሙን ማሳየት በቂ ነው:: ማብራሪያችንን በማጋነን እንዳናቀርብ እንጠንቀቅ:: የአንድን ርእስ ይዘቱንና የመልእክቱን ታላቅነት በማጋነን ብንናገር ሰዎች ይቃወሙናል፤ ዳግም ሊሰሙንም አይፈልጉም:: የሚነገራቸውን ከልባቸው እንዲያደምጡት፥ በተግባር ላይም እንዲያውሉት፥ ካስፈለገም ሐሳባቸውን እንዲገልጹ ለማድረግ ንግግራችንንና አተገባበሩን በቀላል ቋንቋና ዐረፍተ ነገር መናገር አለብን::

በተመሳሳይ ጊዜ ለምንናገረው ርእሰ ጒዳይ ትክክለኛውን መልስና አስተያየት መጠበቅ አለብን:: አድማጮቻችን የምናቀርብላቸው ስብከት አዝናኝ ስለመሆኑ እንዲያደንቁን መጠበቅ አይኖርብንም:: ሕዝቅኤል መልእክቱን ሲያቀርብ ያጋጠመው ችግር ነበር:: ያስተማረው ትምህርት አስደስቷቸዋል የተናገረውን መልእክት ግን ተግባራዊ አላደረጉትም፤ (ሕዝ. 33፥30-32):: አድማጮቻችን የምንናገራቸውን ልብ ብለው እንዲያዳምጡ የጠበቀ ፍላጎት አለን፤ እንዲማሩ፥ እንዲገሠጹ፥ እንዲታረሙ፥ እንዲበረታቱ ማድረግም ይገባናል፤ (2ጢሞ 3:16)::